# “የተቀለበሰው” የኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ጉዞ: የእስር ቤት ማስታወሻዎች

ብርሃኑ ነጋ

## ዝርዝር ማውጫ

## ክፍል 1 ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ለምን?

ሀ. የጽሁፉ አላማ - በዋነኛነት ከግንቦት 97 ምርጫ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያን የዲሞክራሲ ጎዞ መገምገም፣ ለደረሰበት ደረጃ አስተዋጽኦ ያደረጉትን ሀይሎች መለየት እና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታው መስመሩን ይዞ እንዲሄድ መደረግ አለበት ብዬ የማስባቸውን ለመጠቆም ነው:: ከዚህ አንፃር ፅሁፉ አንድም እንደ አንድ ተካፋይ ሒደቱን በተቻለ መጠን በእውነተኛነት ለወደፊቱ ትውልድ መማሪያ እንዲሆን ማቆየት ሲሆን በሌላ በኩል ከዚህ የሚገኘው ትምህርት የወደፊቱ ትውልድ ያሁኑን ትውልድ ስህተቶች እንዳይደግም መሣሪያ እንዲሆን ነው::

ለ. ጽሁፉ የተጻፈበት ጊዜ የነበረው ልዩ ሁኔታ:- እስር ቤት፣ ስለወደፊቱ እርግጠኝነት በሌለበት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የእስር ቤትን ትርፍ ጊዜ ምርታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም ሲሆን ይህን ጽሁፍ በመጽሀፍ መልክ ለማውጣት ግን ቀደም በሎም አላማ ነበር::

ሐ. የተጻፈበት ሁኔታ መረጃዎችን በዘርዝርና በፍጹም እርግጠኝነት ለማውጣት አያስችልም:: ጽሁፉን በተቻለ መጠን እንደወረደ አቅርቦ ምንአልባት እድሉ ተገኝቶ ከእስር ከወጣሁ የሚስተካከለውን ነገር ውጪ ማስተካከል ይሻላል ከሚል ብዙዎቹ ዕውነቶች (facts) ፍጹም ከመረሳታቸው በፊት አሁኑኑ በጽሁፍ ማስቀመጥ ይሻላል ከሚል ነው:: ሥለዚህም አንዳንድ መለስተኛ ስህተቶች (ለምሳሌ ጊዜና ቦታን በእርግጠኝነት ለማስታወስ ወይንም ከሰነዶች ለማረጋገጥ አለመቻል) ቢኖሩ አያስገርምም:: ለማንኛውም ስህተቶቹን ለማሳነስ የሞከራል::

መ. በተቻለ መጠን ጽሁፉን አወንታዊ (positive) ለማደረግ ተሞክሯል:: ምንአልባት በግለሰቦች ላይ የሚነሱ ሂስ መሰል ሀሳቦች ቢኖሩ በተቻለ መጠን ከግለሰቡ ስብእና

ጋር ለማያያዝ ሳይሆን ከተነሱት ሀሳቦች ጋር ለመሟገት ብቻ ነው:: የጽሁፉ ማእከል በአገራችን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ነው:: ይህ እንዲሆን ደግሞ በተቻለ መጠን እውነተኛ መሆንን ይጠይቃል:: እውነተኛው ጉዳይ ደግሞ ግለሰቦችን ሊያስቀይም ይችል የሆናል:: ምን አልባት ይሕ ከተፈጠረ ግን በምንም አየነት ሰዎችን ለመጉዳት ታስቦ የተደረገ አለመሆኑ እንዲታወቅ ያሻል:: ሰው ላለማስቀየም ተብሎ በግልጽ ያልወጣ ቁም ነገር ከግለሰቦቹ መቀየም በላይ የማህበረሰቡን ዕውቀት ስለዚህም ዲሞክራሲያዊ ሂደቱ እንዳይጎዳ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያሻ ግንዛቤ ተወስዷል::

ሠ. ይህ ፅሁፍ በምንም መልኩ የቅንጅቱ ኦፊሴላዊ ግምገማ ወይም ግንዛቤ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም:: የተወሰኑ የቅንጅቱ አመራሮች በዚህ ጽሁፍ ላይ ከተነሱት የተለያዩ ነጥቦች ጋር ልዩነት ሊኖራቸው ይችላል:: ቅንጅቱም አንድ ቀን ይህንን ኦፊሴላዊ ግምገማ ያደርጋል ብዬ እጠብቃለሁ:: ከአመሰራረቱ ጀምሮ ቅንጅቱ የተለያዩ አስተሳሰቦችና አመለከከቶች የተንጸባረቁበትና የሚንጸባረቁበት ነው:: እነኚህን ልዩነቶች ማቻቻል በተወሰነ ደረጃ እየተለመደ የነበረ ባህል ነው:: ያለዚህ ውስጣዊ ድርጅት ባህል ዲሞክራሲያዊ ሥርአት መገንባት አይቻልም:: በዚህ ጽሁፍ ምክንያት የሚንጸባረቁ ልዩነቶች ቢኖሩ የጥንከሬአችን ምልክቶች ተደርገው ሊወሰዱ ይገባል::

ረ. የዚህ ጽሁፍ መለያ እንዲሆን የምሻው ትኩረቱ የወደፊቱ እንጂ የኋላው አለመሆኑ ነው:: የፖለቲካችን ችግር አንዱ ምክንያት ካለፈው ታሪካችን ጠባሳዎች መላቀቅ አለመቻላችን ነው ብሎ መነሳቱ ነው::

## II. ኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ለምን ያስፈልጋታል? ምን ዓይነት ዲሞክራሲ?

ሀ. ነጻነት: ዲሞክራሲና የአገራችን ዋና ዋና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች (ድህነት፣ ንጽህና፣ የተለያዩ በሽታዎች፣ ባህላዊ ችግሮች ወዘተ) በንድፈ ሀሳብ ደረጃና በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ

ሀ.1 የዲሞክራሲ እጦትና የተቋማት ድክመት (ለምን ኢትዮጵያውያን በስደት የበለጠ ምርታማ ይሆናሉ?)

ሀ.2 ነጻነትና የአገራችን ግብርና (የመሬት ይዞታ፣ ማበረተቻ (Incentive) እና የእርሻ ምርታማነት)

ሀ.3 ነጻነት፣ ዲሞክራሲና የአገር ውስጥ ምሁራን (ልሂቃን) ፍጹም ደካማነት። በፍጹም ፍርሀት ቆፈን ከመታሰር እስከስር የሰደደ አድር ባይነት (በጣም እራስን ያሳነሰ የህይወት ትርጉም)

ሀ.4 ነጻነት እንደግብና እንደ እድገት መሳሪያ

ሀ.5 ደሀ አገሮች ዲሞክራሲ ያስፈልጋቸዋል? ምን ያህል ጊዜ መጠበቅ አለባቸው (Even more Urgent)

ለ. ምን አይነት ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ? ስንት ዓይነት ዲሞክራሲ አለ? (በፍሬ ነገር ሁሉም አንድ ነው። በፎርም እንደአገሩ ሊለያይ ይችላል።)

ለ.1 በኢትዮጵያ በዲሞክራሲ ዙሪያ የሚነሱ ጥያቄዎች

- የዲሞክራሲ መሰረት ግለሰብ ወይስ ቡድን? እነኚህስ በተቃርኖ ይቀመጣሉን?
- ዲሞክራሲ፦ አብዮታዊና ሊበራል (በአመለካከት ደረጃ) በእርግጥ ፋይዳ ያለው ክርክር ወይስ ያልተገደበ ሥልጣንን ለመከላከያ የሚቀርብ ማወናበጃ?

ለ.2 ዲሞክራሲያዊ ስርአትን ለመደገፍ የሚችል ማህበራዊ መሰረት (Constituency) በኢትዮጵያ አለን? ማነው ለዲሞክራሲ ሸንጡን ገትሮ የሚታገለው።

ለ.3 ዲሞክራሲና የመንግስት አደረጃጀት በኢትዮጵያ - ፌደራሊዝም ለምን? በምን መስፈርት - ፌደራሊዝም ለመልካምና ለተቀላጠፈ አስተዳደር ወይንስ ለዘር ልሂቃን አቋራጭ ስልጣንና ንብረት ማከማቻ?

ለ.4 ዲሞክራሲ፣ ሰላምና መረጋጋት በኢትዮጵያና በአካባቢዋ አገሮች

ለ.5 የብሄርተኞችን ፍርሀት ከምን መውሰድ? በታሪክ የታዩት ችግሮች እንዳይደገሙ መፍራት ወይንስ ይህንን ፍርሀት ለጊዜያዊና ለግል መጠቀሚያ ማድረግ?

## III. ዲሞክራሲያዊ ስርአት በኢትዮጵያ ለመገንባት የሚገጥሙ ዋና ዋና ችግሮች

- በአጠቃላይ የዲሞክራሲ ስርዐት ግንባታ ችግሮችን በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል:: የመጀመሪያው በጊዜው ካለው መንግስት ምንነት ውጪ በአጠቃላይ ከባህላችንና (በተለይ ለስልጣን ካለን አመለካከት) ከታሪካችን ጋር የተያያዘና ምን አልባትም በመንግስት ሥልጣን ላይ ያለው ሀይል ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን መገንባት ከልቡ እንኳን ቢፈልግ የሚገጥሙትን ችግሮች ታሳቢ የሚያደርግ ሲሆን፡ ሁለተኛው ደግሞ በመንግስት ስልጣን ላይ ያለው ሀይል ለእውነተኛ ዲሞክራሲ እንቅፋት ሊሆን የሚችልባቸውን ምክንያቶች የሚያይ የሆናል::

### 1. አብዛኛው ሕብረተሰብ ስለስልጣን ያለው አመለካከት

ሀ. ለአብዛኛው ሕዝብ መንግስት ማለት ምን ማለት ነው? ምንም ያልተገደበ ስልጣን ያለው በየትኛውም ሕይወታችን መግባት የሚችል ሀይል ተደርጎ መወሰዱ:: ለዚህም ዋናው ምክንያት የራሳችን የቅርብና የሩቅ ጊዜ የፖለቲካ ታሪክ መሆኑ (the power we know is absolute power)

ለ. ለስልጣን ብቻ ሳይሆን ለባለስልጣንም ያለን አመለካከት (በመንግስት ብቻ ሳይሆን በእለት ተእለት ኑሮአችንም (a very hierarchial society) ስለዚህም ለጉልበተኛ እንመቻለን::

ሐ. ከዚህ ጋር የሚያያዘው ግለሰቡ ስለራሱና ስለኑሮው ያለው ፍጹም ዝቅተኛና በራሱ ህይወት ላይም ምንም ሥልጣን የሌለው አድርጎ ማመኑ (a complete sense of powerlessness) ስለዚህም የሚጠብቀውም በጣም አነስተኛ ነው (Low expectation)

### 2. ከታሪካችን ጋር ያለን ፀብ (ወይንም ምንም ያልተገራ አድናቆት)

- ብዙው የፖለቲካ እምነቶች ውይይቶች አሁንም ቅድሚያ የሚሰጡት የጋራ የሆነውን ያሁኑን የአብሮ መኖር ችግሮችን እንዴት እንደምንፈታ ሳይሆን ያለፈውን የታሪክ ጠባሳዎች ላይ መሆኑንና ይህም አብሮ የሚያመጣውን ስሜታዊነት በአምክህኖት ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ውይይትን አዳጋች ማድረጉ
- ይህም ወጥ የሆነ የጋራ አገራዊ ራዕይ ለማበልጸግ እንቅፋት መሆኑ
- ደካማ ግለሰብነት (Weak Individualism ) ባህላዊ? ፖለቲንዊ?
- በጣም ደካማ ወደፊት የመመልከት ባህል:: በዚህም ምክንያት የወደፊቱን ለማስተካከልና በዚህም በጋራ መጠቀም (ለወደፊቱ ትውልድ) ላይ መሠረት ያደረገ የወደፊቱን የማስተካከል ውይይት አለማድረግ በራሱ የጋራ ድክመት መሆኑ ብቻ ሳይሆን ከጋራ እድገት የጋራ ጥቅም ሊያስገኝ የሚችል ድምሩ አውንታዊ (Positive sum) ከሆነ አመለካከት ይልቅ የፖለቲካም ሆነ ሌሎች የጋራ ሕይወታችን ድምሩ ዜሮ እንደሆነ ጫወታ ማየት::

## 3. ፍጹም ሰነፍና ጨለምተኛ መሑራዊ ባህል (Lazy and Cynical intellectual culture)

- “የደብተራ” ባህል? እውቀት የሚሸመደድና ካለፈም ቴክኒካዊ እንጂ የተመራማሪውን ሂሳዊ አስተሳሰብ (Critical thinking) የሚንጸባረቅበት አለመሆኑ
- እውቀት ከራስና ከማህበረሰቡ ህይወት ጋር ግንኙነት ያለው ነገር ባይሆንና ዝም ብሎ የኑሮ መደጎሚያ አድርጎ መውሰድ (የህግ፣ የፖለቲካ ሳይንስ፣ ... ወዘተ በምሳሌነት)
- ሥር የሰደደ የጨለምተኛነት (Cynical) አመለካከትና ይህንን ጨለምተኛነት ለግለሰቡ ምሁራዊ ስንፍና (Intelectual Laziness) መሸፈኛ አድርጎ መጠቀም
- የሙያተኛነት ሥሜት (Professionalism) መሞት (መምህራን ስለ ትምህርት፣ ሀኪሞች ስለ ሕክምና ጠበቆች ስለ ሕግ ... ወዘተ ያላቸው አመለካከትና በዚህ ሙያ ውስጥ ስለ እራሳቸው ያላቸው አመለካከት
- ይህ ሁሉ የፈጠረው የዝቅተኛነት ስሜት ምሁራን የማህበረሰቡን ችግሮች የሚያሳዩ፣ የወደፊት ኑሮው የተሻለ እንዲሆን የሚጠቁሙ ሀይሎች መሆናቸው ቀርቶ እንደማንኛውም ያልተማረ ዜጋ አርግ የተባሉትን የሚያደርጉ፣ ለራሳቸውና ለሙያቸው ብዙም ክብር የሌላቸው ደከማ ዜጎች መሆናቸውና በዚህም መላውን ሕብረተሰብ አብረው እንዳዳከሙት::

- በተወሰነ ደረጃ ግን እነኝህ ችግሮች የመጡት በአገራችን ከተፈጠሩት መንግስቶች ምንነት ምክንያት ነው፡፡

## 4. በኢትዮጵያ ያለው መንግሥት ለዴሞክራሲ ግንባታ ዋነኛው እንቅፋት

**(ሀ) በጣም አጭር ግምገማ ሥለ ቀድሞው መንግሥቶች (የኃይለስላሴ ዘመን)**

**ሀ.1** ኃይለስላሤና መለኮታዊ ሥልጣን፡ የዘመናዊነትና ያልተገደበ ዘውዳዊ ሥልጣን ፍላጎት ግጭት፡፡ የሥልጣን እብደት እስከ መጃጀት፡፡ ለልጅ እንኳን መስጠት አለመፈለግ

**ሀ.2** የጸረ- ዘውድ ትግሉ ዴሞክራሲያዊ ለመሆን ለመቻል፡፡ በጊዜው የነበሩ ከዘውዱ መሻሻል የሚጠቀሙ ልሂቆች ዘውዱን ለማሻሻልና ትንሽም ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ ፍላጎትም ችሎታም ማጣት፡፡

**ሀ.3** ምንም አይነት የዴሞክራሲ ትግል አለመብቀልና የውይይት ሜዳው ለሶሻሊትቶች መለቀቅ

### ለ. የደርግ ዘመንና የፈጠራቸው ችግሮች

**ለ.1** የደርግ ሶሻሊዝም የሚሰራ ርዕዮተ አለም ወይንስ የተመቸ የመግዢያ መሳሪያ

**ለ.2** ሶሻሊዝም የሚሰጠው ጠንካራ ድርጅታዊ መሠረት በወታደር እጅ የሚገባ

**ለ.3** ሶሻሊዝምና የቁጥጥር ፍቅር (ለመግዛት የዜጎችን መሠረታዊ ሕይወት ሁሉ በቁጥጥር ማግባትና ግለሰቡን ፍጹም የመንግስት ጥገኛ ማድረግ (በገጠርና በከተማ በኢኮኖሚ በማህበራዊና በፖለቲካ ህይወት) ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚመጣ የሙስና ችግር፡፡

**ለ.4** አምባገነንነት ለመግዛት የህዝብ ነጻነትና ነጻ መንፈስ ሳይሆን ፍርሀትና መሸማቀቅ ነው የሚያስፈልገው፡፡ በአጠቃላይ አምባገነንነት የሚፈጥራቸውና የሚያበለጽጋቸው መጥፎ ባሕርያት (ፈሪነት፣ አደርባይነት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ እራስን አቅልሎ ማየት (በራስ አለመተማመን ) ፣ ምቀኝነት ፣ በሰው ችግር እራስን ከፍ ማድረግ፣ መዋሸት ... ወዘተ)

**ለ.5** ይህም የህብረተሰቡን ደካማ ክፍል (በእውቀት፣ በጸባይ ... ወዘተ) የማህበረሰቡን መሪ ቦታ እንዲይዝ ይፈቅድለታል ብቻ ሳይሆን ሌላው እንዲጠጋውም አይፈልግም፡፡

**ለ.6** ሶሺያሊዝምና ፕሮፖጋንዳ

## (ሐ) ኢሕአዴግና ልዮ የሚያደርገው ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ፀባዮቹ

ኢሕአዴግ ከራሱ ታሪክና ከተፈጠረባቸው ሁኔታዎች አንፃር በአገራችን ምንአልባትም ከሌሎችም አገሮች አንፃር ልዮ የሚያደርጋቸውና ለእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ እንቅፋት እንዲሆን የሚያደርጉት ልዮ ባህሪዎችአሉት:: እነኝህም ባህሪዎቹ ከራሱ አፈጣጠር ጋር የተያያዙ ሶስት ሁኔታዎች የፈጠሩአቸው ናቸው የሚል እምነት አለኝ:: ሥለዚህም ከነኝህ ሶስት ሁኔታዎች የተወረሱትን ፀባዮቹን ለየብቻ መመልከት ይጠቅማል::

### ሐ.1 ኢሕአዴግና የግራ (የኮሙኒስት) ርዕዮተ አለም

- የተፈጠረው የግራ ርዕዮት የበላይነቱን በያዘበት ጊዜ በተፈጠሩ ወጣቶች እንዲሁም ይህንን ርእዮተ አለም ከምር መውሰድ ብቻ ሳይሆን እንዲያውም የማክረር ታሪክ አለው::
- ከግራ ርዕዮት ከወሰዳቸውና ለስልጣኑ ዘመን መጠቀሚያ ካደረጋቸው ነገሮች አንዱ ህብረተሰብን የግለሰቦች ስብስብ ሳይሆን የግሩፕ ስብስብ (መደብ፣ ፆታ፣ ብሄር፣ ... ወዘተ) አድርጎ በዋናነት መውሰዱ (ይህም ከሚታየው ዴሞክራሲ ጋር ያለው ዝምድና)
- የግራ ርዕዮተ አለሙና አደረጃጀቱ (እራሱ በድርጅቱ ውስጥ ያለው አወቃቀርም ሆነ ህብረተሰቡን የሚያደራጁበት አካሄድ):: በደርጅቱ ያለው እምነትና የግለሰቡ ተገዢነት
- ፍፁም የሆነ የቁጥጥር ፍቅሩ (Control Freak) እሱ ለማይቆጣጠረው ምንም አይነት አደረጃጀት ያለው ጥርጣሬ
- የግራ ርዕዮተ አለም ለኢኮኖሚና በፖለቲካ ትስስር መካከል ያለው አመለካከትና የራሱን የኢኮኖሚ አቅም በማዳበር (የድርጅቱን) በአንፃሩ ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ያለው ጥርጣሬ
- በግብ እና በመሣሪያ (end and means) ያለው አመለካከት:: ለአላማው ግብ ምንም አይነት መሣሪያ ተቀባይነት ያለው መሆኑ (በጉልበት፣ አፈና፣ ፀረ ዴሞክራሲያዊነት... ወዘተ) በራሳቸው ችግር የለባቸውም አላማው ትክክል እስከሆነ::

### ሐ.2 ኢሕአዴግና የዘር ብሄርኝነት (Ethnic Nationalism)

- የኢሕአዴግ መሪ ድርጅት (ህወሀት) የዘር ፖለቲካ ይህ ከግራ ርዕዮቱ ጋር የፈጠረው ችግርና ሁሌም አብሮት የሚኖረው ፍትጊያ (tension):: ማርክሲዝምና ብሄርተኝነት ሲጋጩ በታሪክ የትኛው ያይላል?
- የዘር ብሄርተኝነት የሚሰጠው ቅድሚያ የግራ ርዕዮተ አለም የሚሰጠው ቅድሚያ::
- ቋንቋና ባህል ከመሠረታዊ የዴሞክራሲ መርሆዎች (በዜግነት ላይ የተመሠረቱ) ጋር ሲጋጭ የሚፈጥረው ችግር::
- ዜግነትና ዘውጌ (ብሔር) ከመሠረታዊ የዴሞክራሲያዊ ሥርአት መርሆዎች አንፃር ሲታይ (መንግሥት ዜጎቹን እንዴት ያያቸዋል? እንደ ግለሰብ (ዜጋ) ወይንስ እንደ ግሩፕ (ዘውጌ)
- በዘውጌ ላይ የተመሰረተ መንግስት በአናሳ ዘውጌ እጅ ሲያዝ ወይንም ተይዟል ተብሎ በሚታሰብበት የተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ሥርአት መፍጠር ይቻላል? (Ethicity & Stable democracy)
- የአገር ሀብት ክፍፍል እውነትና የህዝብ ሥሜት (Perception and reality) በዘውጌ የተከፋፈለ የፖለቲካ ሥርዐት ውስጥ የሚገጥሙ መሠረታዊ ችግሮች::
- የዘውጌ ፖለቲካና የመንግስት የጋራ ተቋማት:: የዴሞክራሲ ግንባታ የተቋማት ጥንካሬና ነጻነት አስፈላጊነት በአንድ በኩልና የዘውጌ ፖለቲካ የሚፈጥረው ችግር (ለምሳሌ ለተቋሙ እንቅስቃሴ የሚያስፈልግ የሰው ሐይል በመመልመልና በማቆየት በኩል)

ሐ.3 የአለም ሁኔታ መቀየር፣ የሀብታም አገሮች አስፈላጊነትና ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት መሠረታዊ የኢህአዴግ እምነቶች ጋር ያለው ግጭት:: ለዚህም የሚያስፈልገው ብልጥነትና ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄደው የተለያዩ የተቃርኖ ገጽታዎች (Schiz-phrena)

- የውጭ የገንዘብ እርዳታ ከአስፈላጊነት ለስልጣን ለመቆየት
- ለመግዛት በገበያና በካፒታሊዝም መማል አስፈላጊነትና ከግራው ርዕዮት ጋር ያለው ቅራኔ
- ለመግዛት በዴሞክራሲ መማል አስፈላጊነትና (በዜግነት ላይ የተመሰረተ) የህም ከግራው ርዕዮትም ሆነ ከብሄርተኛነቱ ጋር የሚፈጥረው ገጭት

- አይን ያወጣ አምባገነንነት ለመግዛት አስቸጋሪ መሆኑ በዚህም ምክንያት የህግ ተቋማትን የመግዢያ መሳሪያ አድርጎ ለመጠቀም መሞከርና ይህም የሚፈጠረው ተቋማዊ ቀውስ
- የመሰረታዊ እምነትና ለህዝብ የሚገለፅ ሰውነት (public personnel) መጋጨት የሚፈጥረው አስከፊና አይን ያወጣ ውሸታምነት (በፕሮፖጋንዳ ብቻ ሳይሆን በመሪዎቹ ማንነት ላይ)
- ብሄርተኝነት የሚፈልገው የራስን ብሄር መጥቀም በአንድ በኩልና የፖለቲካ አገዛዙ የሚፈልገው "የብሄር እኩልነት ተአማኒነት" የሚፈጠሩት ግጭት:: የግድ ለብሄሩ ጥቅም ብቻ የቆሙ ብሄርተኞችን በዘላቂነት ለማታለል አለመቻልና ሥለዚህም ለብሔሮቹ "ተለጣፊ በሄርተኞች" የማዘጋጀት አስፈላጊነት:: የዚህ ግን ዘላቂነት ማጣት:: የሌላው መግዛትን ብቻ ማእከል ያደረገ አካሔድ::

## (5) የክፍል አንድ መደምደሚያ

- እነኝህ ችግሮች ባሉበት ሁኔታ እውነተኛ ዴሞክራሲ ሕልም ነው ወይስ ሊሆን የሚችል ሥርአት?
- ከእንቅፋቶቹ ሁሉ ትልቁ የመንግሥት እምቢተኛነት መሆኑና በዚያ ላይ ያሉት ጋሬጣዎች ከተነሱ ሌሎች ችግሮች በጊዜ ብዛትና በትምህርት ሊወገዱ የሚችሉ መሆናቸው
- የህብረተሰቡ የዴሞክራሲና የነጻነት ጥማት በምርጫው ጊዜ እንደታየው እድሉን ካገኘ በነጻነት ለመኖር የሚፈልግ ብቻ ሳይሆን የሚመኝ መሆኑ
- እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በጣም የተወሣሰቡ ማህበራዊ ችግሮች ባሉበትና የፖለቲካ ሕይወታችን በእርስ በእርስ ጥርጣሬ (በተለይ በዘርና በሀይማኖት) በታጠረበት አገር የተረጋጋና ወደ ብልፅግና የሚያመራ ሕይወት ለመኖር ሁሉም ከሚያምንበትና ከእውነተኛ ዴሞክራሲ ሌላ ምን አማራጭ አለን?
- የመንግስታችን በተለይ ደግሞ የኢሕአዴግ ባህርይ ከላይ የተጠቀሰው አይነት ከሆነ ኢህአዴግ እውነተኛ ዴሞክራሲ በሰላማዊ መንገድ ለማምጣት ይተባበራል ተብሎ ለምን ታሰበ? የዋህነት? ወይንስ መሠረት ያለው ሥሌት? በተለይ ይህ እንደማይሰራ በግልፅ የሚናገሩ ሰዎችና ድርጅቶች በሞሉበት አገር

*ከ14 አመት ሥልጣንና በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚታየው ግልጽ ቅራኔ አንፃር ኢህአዴግ በአጠቃላይ መለስ በተለይ ለሌላቸው ታሪክና ዝና በተለይም በአለም አቀፉ ሕብረተሰብ ዘንድ ካላቸው ተቀባይነት አንጻር በአገሪቱ ዴሞክራሲ ማምጣትን እንደግባቸው ይቆጥሩታል (የተሳሳተ?) ግንዛቤ!

- *መሸጋገሪያ* (Paragraph) *ስለሚቀጥለው ክፍል ሁለት*

# ክፍል 11: የግንቦት 97 ምርጫ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ለዴሞክራሲ ጮራ ለምን ፈነጠቀ

## የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስከ ምርጫ 97 ድረስ

I. *ቅድመ ምርጫ 97 የኢትዮጵያ ፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታ*

1. *የመጀመሪያዎቹ አመታት የኢህአዴግ የጫጉላ ሽርሽር ዘመን*

ሀ. ሰላም የናፈቀው ሕዝብ ከነጥርጣሬው ኢሕአዴግን ተቀብሎት ነበር ወይንም እድል ለመስጠት ፈቃደኛ ነበር

ለ. የዴሞክራሲ መሬ፣ የነጻ ጋዜጦች መለቀቅ ... ወዘተ ወደ ዴሞክራሲ ሊወሰድ የሚችል እርምጃ በሚል በአወንታዊ መልኩ ማህበረሰቡ ተቀብሎት ነበር። (የህገ መንግስቱ ሁኔታ... ወዘተ)

ሐ. በመጀመሪያ ጊዜ የወጣው የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ከእዝ ኢኮኖሚ መላቀቁን ማሳየት፣ (ምንም እንኳን ብዙዎቹ ማሻሻያዎች የደርግን የመጨረሻ የቅይጥ ኢኮኖሚ ፕሮግራም ጋር ቢመሳሰሉም) በዚህም የውጭ ድጋፍ ማግኘቱ (ስለዚህም የውጭ ምንዛሪ ችግር መቀረፉ) ብቻ ሳይሆን በፍጹም ታፍኖ የነበረውን የግል ኢኮኖሚ ዘርፍ በሰፊው እንዲንቀሳቀስ ማስቻሉ፣ የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት በመጀመሪያዎቹ ጥቂት አመታት ፈጣን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መታየት ይህ ሁሉ ለኢሕአዴግ ደጋፍን ማስገኘት

መ. በዚህ ጊዜ (የመጀመሪያዎቹ 5-6 አመታት) በመንግስት ላይ የነበረው ተቃውሞ በዋነኛነት በሚከተለው የብሔር ፖሊሲ፣ በኤርትራ ላይ የወሰደው አቋምና በተለይ በአንዳንድ ቦታዎች በነበረው የጎሳ ግጭት ወይም ደግሞ እንደ አርባጉጉ

በመሰሉ ቦታዎች በተፈጸመው ገጭት ምክንያት በወደፊቱ የአገሪቱ የአብሮ መኖር ሁኔታ ላይ የነበሩ አለመተማመኖች (anxiety)

## (2) የጫጉላው ሽርሽር ሲያልቅ የኢሕአዴግ ፖለቲካ እያደር ተአማኒነት ማጣት

(ሀ) የኢኮኖሚ ማሻሻያ (Reforms) ውጤታማነት መቀዝቀዝ (Reaching its limits) የኢሕአዴግ የግራ አመለካከት ለማሻሻያዎቹ ማእቀብ መሆን፤ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማዝገም፣ የእርሻ እንቅስቃሴ በዚያ ዙሪያ የሚደረጉት ማሻሻያዎች መንጠፍ የከተማው ሥራ አጥነት መጨመር

(ለ) ከኤርትራ ጋር የተፈጠረው ግጭትና ይህ የፈጠረው የኢሕአዴግ የውስጥ ትርምስ

(ሐ) በጦርነቱ ኢሕአዴግ ያገኘው እድልና የዚህ እድል መኮላሸት ሕዝብ በኢሕአዴግ ላይ ያለው ጥርጣሬ እያደር እየጨመረ መሄድ::

(መ) የኢሕአዴግ ምርጫ ተብዬዎች ዴሞክራሲያዊነትን የሚያረጋግጡ ሳይሆኑ ጥያቄ ውስጥ የሚከቱ መሆናቸው (በተለይ የ1992 (2000) ምርጫ)

(ሠ) ለመሆኑ ሰላምና መረጋጋት በእርግጥ አለ? የክልል ግጭቶች (ጋምቤላ አዋሳ ከፋሽካ... ወዘተ)

## (3) ለምን ጠንከራ ተቃዋሚ መፈጠር አልቻለም?

(ሀ) የኢሕአዴግ የዘር ፖለቲካ ስኬት

(ሀ-1) የዘር ፖለቲከ የመንግስትን ልዩ ፈቃድ ማግኘት በየብሔሩ ላሉ ንዑስ ከበርቴዎች የሥልጣን መወጣጫ አቋራጭ ሆኑላቸው:: ስለዚህም በኢህአዴግ የመጀመሪያው ዘመቻ የተፈጠሩት ድርጅቶች አብዛኞቹ የብሄር ድርጅቶች ነበሩ

(ሀ-2) ኢሕአዴግ ሆን ብሎ ህብረ ብሄራዊ ድርጅቶችን ያዳክምና ያንኳስስ ነበር:: የዚህ ውጤት በውስጡ የነበሩትን ህብረ ብሄራዊ ድርጅቶች ራሳቸውን ወደ ብሄር ድርጅት ቀየራቸው (ኢሕዴን - ብአዴን)

(ሀ-3) ሕብረ-ብሔራዊ ስሜትና አመለካከት አለን የሚሉ ሰዎች እንኳን በተፈጠረው ሁኔታ ብሄራችንን እናድን በሚል የብሄር ጨዋታው ውስጥ ገቡበት (ምሳሌ

ፕሮፌሰር አስራትና መኢህድ፣ በደቡብ ህብረት ውስጥ የተደራጁ አንዳንድ ሰዎች ... ወዘተ)

(ሀ-4) ኢሕአዴግ ማህበረሰቡ በብሔር ድርጅቶች እንዲደራጅ ቢፈልግም ነፃ የብሔር ድርጅቶች እንዲኖሩ አለመፈለጉ ብዙ ደካማ የብሄር ድርጅቶች እንዲፈጠሩና በብሔሮችም ውስጥ ሥር የሰደደ መከፋፈል እንዲፈጠር ማድረጉ፡፡

(ለ) የአገሪቱ ልሂቃን ከፖለቲካው ፍጹም ማፈግፈግ

(ለ-1) ፖለቲካው በዘር ላይ ማተኮሩ ሰፋ ያለ አመለካከትና ራዕይ ያለውን የህብረተቡን ልሂቅ ከፖለቲካው ማራቅ

(ለ-2) በልሂቁ አከባቢ ሊነሱ የሚችሉ የፖለቲካ አመለካከቶችን በቶሎና በሀይል መምታት (የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና መምህራን) ወይንም ደግሞ ተለጣፊ ድርጅቶችን በመፍጠር ማዳከም (የሰራተኛ ማህበር፣ የመምሕራን ማህበር... ወዘተ)

(ለ-3) ሕብረተሰቡ በደርግ ሽብር ምክንያት ከገባበት መሸማቀቅና ፍርሀት ሙሉ ለሙሉ እንዳይወጣ በጉልበት ብቻ ሣይሆን በመሰረታዊ ኑሮው ማስፈራራት (ከስራ ማባረር፣ ከንግድ ማፈናቀል ... ወዘተ) ይህም በተለይ ልሂቁን ከፖለቲካ እንዲሸሽ ማድረጉ

(ሐ) በግልፅ የተቀመጠ አሰባሳቢ ራዕይ መጥፋቱ

(ሐ-1) የተቀመጠውን የብሔር ራዕይ በግልጽ የሚያጋልጥና የሚተካ አማራጭ ራዕይ ከየትኛውም የህብረተሰብ ክፍል በግልጽ አለመቅረቡ፡፡ በአብዛኛው ተቃውሞው በጥላቻ ላይ የተመሰረተ እንጂ ከስር መሰረቱ የኢህዴግ አመለካከት በሚተካ አወንታዊ ራዕይ እስከ ግንቦት ምርጫ ድረስ ቀርቧል ለማለት ያስቸግራል፡፡

(ሐ.2) በዚህም ምክንያት የፖለቲካ ሐይሎችን ማሰባሰብና ያሉትን በጋራ ለማሰራት በፍጹም አልተቻለም ነበር፡፡

**(4) የውጪው አለም የኢሕአዴግን የዴሞክራሲ ማጭበርበሪያ እያወቀበት መሄድ**

(ሀ) በየቦታው የተከሰቱት ግጭቶችና የሰብዊ መብቶች ጥሰቶች ለውጭው አለም እያደር እየከበደ መሄዱና የውጭ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ተደጋጋሚ ቅዋሜ (ጋምቤላ፣ የተማሪዎች ድብደባ፣ ... ወዘተ)

(ለ) ይፈጠራሉ የተባሉት የዴሞክራሲ ግንባታ ተቋሞች ሆነ ተብሎ አለመቋቋምና መጠናከር አለባቸው የሚባሉት እያደር እየተዳከሙ መሄድ በእርዳታ ሰጪዎች ዘንድ እያደር እየፈጠረ የሄደው ጥርጣሬ (የእንባ ጠባቂና የሰብዊ መብት ኮሚሽኖች መቋቋም፣ የብሮድካስት አዋጅ ተግባራዊ አለመሆን፣ የፍትህ ተቋማት ፍፁም የመንግስት መሣሪያ መሆን እያደር መጋለጥ (የስዬ አዋጅ ... ወዘተ) የሲቪክ ማህበረሰብ ተቀማትን ሆን ብሎ ማዳከምና አንዳንዱን ማገድ **(EWLA, EHRCO... etc)**

(ሐ) በኢሕአዴግ ላይ እየተሰማ ያለው ተቃውሞ እያደር እየጎላ መሔድ

(መ) በኤርትራ ጦርነት ምክንያት የተፈጠረው ቅያሜ

(ሠ) እርዳታ ሰጪዎች የጠበቁቸው የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች መዘግየትና **(Privatization)** በእያንዳንዱ ላይ እንደውም ግልፅ የሆነ የመንግሥት እምቢ ባይነት **(Financial Sector, Telecomunication... etc)**

(ረ) እንደ መሬት ይዞታ ባሉ ወሳኝ ጥያቄዎች ላይ የመንግሥት ግትር የግራ ፀባይ በግልፅ መውጣቱ የፈጠረው ጥርጣሬ

(ሰ) በአጠቃላይ የእርዳታ ሰጪዎች በመንግስት ላይ የነበራቸው ያልተገደበ እምነት እያደር እየተሸረሸረ መሄድና የተጠበቀውም ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት ሩቅ ሊሄድ እንደማይችል መገንዘብ:: በነኝህ ሁሉ ምክንያቶች የተወሰነ የፖለቲካ ማሻሻያ ማስፈለጉን መገንዘብ (በአመለከከት ደረጃ መልከም አስተዳደር የለጋሽ አገሮችን ቀልብ መሳቡ)

(ሸ) በነኝህ ሁሉ ምክንያቶች ግልጽ የፖለቲካ ማሻሻያ መጠየቅ፣ በተለይም የግንቦቱን ምርጫ ዴሞክራሲያዊ ማድረግ የለጋሾች እንደግብ ያስቀመጡት አንድ አላማ መሆኑ::

# II. የኢሕአዴግ ቁማር (የኢሕአዴግ በራስ መተማመን የፈጠረው ሠህተት)

ኢህአዴግ በተለያየ ግፊት ምክንያት የግንቦቱን ምርጫ “ዴሞክራሲያዊ” ለማድረግ አንዳንድ እርምጃዎች ሲወስድ ሁለት ወፍ በአንድ ድንጋይ እንደሚመታ እርግጠኛ

ነበር፡፡ ይኸውም በአንድ በኩል ጥያቄ ውስጥ የገባውን የራሱን ዲሞክራሲያዊነት በተለይ በለጋሾች ዘንድ ማረጋገጥ በዚያውም የመንግስትን ተቀባይነት (Legitimacy) ማስፋፋት በዚያው ልክ ግን ምርጫውን በሰፊ ልዩነት እንደሚያሸንፍ (ያለ ብዙ ማጭበርበር) እርግጠኛ ሆኖ ነው፡፡ ይህ ክፍል በዚህ የተሳሳተ ስሌቱ ምክንያት የሆኑትን ቁምነገሮች መዘርዘር ነው፡፡ (በዚህ ላይ የኢሕአዴግ ስብሰባዎች ቃለጉባኤ በሌለበት ለትንተናው መሰረት የሆኑት በተግባር ያሳያቸው ፀባዮቹ ናቸው፡፡ እንዲሁም በጊዜው ከአንዳንድ የኢሕአዴግ አባሎች ጋር በተደረጉ ውይይቶች)

(1) በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሀይል አሰላለፍ በኢሕአዴግ እይታ

(ሀ) በዋናነት ኢሕአዴግ ያየው የገጠር/ከተማ ልዩነት በገጠር ያለው ሕብረተሰብ ይደግፈናል የሚለው ሥር የሰደደ እምነታቸው (ለምሳሌ መለስ ከዩኒቨርሲቲ አስተማሪዎች ጋር ባደረገው ውይይት የተናገረው) ገጠሩን በሙሉ እናሸንፋለን ብለው እንዲያስቡ አድርጓቸዋል፡፡

(ለ) ሁለተኛው አመለካከት የብሄር አሰላለፍ ነው፡፡ በዚህም ሳቢያ እርሱ በሚያይበት የጭቁን ጨቋኝ ብሄር ልዩነት (dycotomy) ምናልባት በአማራው ብሔር ካልሆነ በቀር በሌሎች ክልሎች ያለምንም ጥርጥር አሸንፋለሁ የሚል ግምት ነበረው (ምናልባት የኦሮሞ ችግርም ቢኖር ትንሽ ድጋፍ ያለው ኦነግ ነው እሱም ምርጫው ውስጥ ስለሌለ ችግር አይሆንም የሚል ስሌት)
- የተሳሳተ የብሔርተኝነት ስሌት

(ሐ) በከተሞች ትንሽ ችግር ሊገጥም እንደሚችል ቢገመትም ይህም ቢሆን በተለይ በሚያሳስቡት የወንድ/ሴት ልዩነት (dychotomy) ሴቶች በአብዛው ኢሕአዴግን የደግፋሉ የሚል አሁንም የተሳሳተ ስሌት ነበራቸው፡፡

(መ) ከዚህ በተጨማሪ በከተሞችም ቢሆን በመደብ ደረጃ ድሀውና በተለይ ሰራተኛው ሕዝብ እኛን ይደግፋል የሚል ከግራ እምነታቸው የመጣ አመለካከት የነበራቸው ይመስለኛል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ስሌት የአብዛኛ ውን ሕዝብ ድምፅ እናገኛለን የሚለው እምነታቸው ሥር የሰደደ ነበር፡፡

(2) ኢሕአዴግ ስለ ድርጅት ያለው አመለካከትና የዲሞክራሲ ዘብራቃነት

(ሀ) እንደማንኛውም በግራ ርዕዮተአለም እንደተጠመቀ ድርጅት ኢሕአዴግ በድርጅት ጥንካሬና ዲሲፕሊን በጣም ያምናል:: የእራሱን ድርጅት ብቻ ሳይሆን ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በራሱ አምሳያ በማደራጀት (ሰራተኛ፣ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ … ወዘተ) ህብረተሰቡን በነኚህ መሳሪያዎች እቆጣጠራለሁ ብሎ ያምናል:: ሥለዚህም በፖሊሲው፣ በእምነቱ፣ በአሰራሩ፣ … ወዘተ ህዝብ በግሉ ምን ይላል ከሚለው ይልቅ በእነኝህ ድርጅቶች እንቅስቀሴ ይመካል:: ለህዝብ ግለሰባዊ ስሜቶችና እርምጃዎች ብዙ ግምት አይሰጥም:: ዴሞክራሲ ደግሞ ትንሽ ዘብራቃ ነው::

(ለ) በዚህም ምክንያት በአጠቃላይ ስለህዝቡ ያለው መረጃ በእኝህ ድርጅቶች አመራሮችና ከካድሬዎቹ የሚያገኘው ብቻ ነው:: ይህ ደግሞ እራሱን የቻለ መሠረታዊ ድክመት አለው:: ከካድሬዎቹም ውጪ ያሉት አድርባይ ደጋፊዎቹ የሚሰጡት መረጃ እንዲሁ የተሳሳተ ነው::

(ሐ) ከዚህ አልፎ (ከዚህ ጋር በተያያዘም) በተወሰነ ደረጃ ኢሕአዴግ የራሱን ፕሮፖጋንዳ በካድሬዎቹና በዝቅተኛ አባሎቹ ብቻ ሳይሆን በአመራር ደረጃም ማመን ተጀምሮ ነበር (ለምሳሌ በረከትና በቴሌቪዥን የሚታዩት የኢትዮጵያ ገበሬዎች)

(መ) በዚያው ልክ ኢሕአዴግ ስለ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያለው እይታና እነሱንም የሚለካበት መስፈርት ለስህተቱ አስተዋጽኦ አድርጓል::

- ድርጅታዊ ድክመታቸውን በስለሳ ያውቃል ይህንንም በቀጥታ ከምርጫው ድክመት ጋር አያይዘውታል::
- በውስጣቸው ያሉትን ልዩነቶች በጣም አጉልቶ አይቷቸዋል (የተጣጠፉ ድርጅቶች)
- ለአመራሮቻቸውም ከፍተኛ ንቀት አለው:: በዙዎቹን የሥልጣን ፍርፋሪ ከሚፈልጉ ወይንም የዘር ጠላቻ ካላቸው በላይ ለዴሞክራሲ የቆሙ ናቸው ብሎ አያምንም:: ከራሱ መሪዎች ጋር አነጻጽሮም (በግለሰብ ደረጃ) እሱ የተሻለ መሆኑን ያምናል::
- ለችሎታ የሚሰጠውን ግምት (በመሪዎቹና በካድሬዎቹ) ካላቸው የእምነት ጥንካሬ ጋር አያይዞ አያየውም

(3) በዚህ ሁሉ ምክንያት ኢሕአዴግ ላልታሰበ አጋጣሚ በቅጡ አልተዘጋጀም::

(ሀ) በድርጅቱ ጥንክሬ ስለተመካና ማሽነሩ እርግጠኛ ስለሆነ ለሚፈጠር አጋጣሚ (ለመስረቅ) የመንግሥት ሀይሎቹን በመጀመሪያ አላዘጋጀም በዚህም ምክንያት አሰራረቁ በጣም የቀሽም እንዲሆን አድርጎታል

(ለ) የመንግሥት ሥልጣኑንና ተቋማትን መጠቀም ሲጀምር (ለምሳሌ የምርጫ ቦርድን በማጣራት ሒደቱ) ብዙ ነገሮች ከእጁ ወጥተው ነበር

(ሐ) ከሁሉም በላይ ግን ማንኛውም በዴሞክራሲያዊ ሂደት የሚያምን ሐይል በትንሹም እንደሚያውቀው በውጤቱ ፍፁም እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ ስለዚህም ድንገት ሁኔታው ከጠበቁት ውጪ ቢሆን ለስላሳ መውደቂያ አማራጮች (Soft Landing) አላዘጋጁም ብቻ ሣይሆን በፍጹም አልታሰበበትም፡፡ (ለምሳሌ ከተቃዋሚዎቹ ጋር በምን ሁኔታ አብሬ ልሰራ እችላለሁ የሚል ስሌት በፍጹም አልነበረውም)

(መ) ሥለዚህም ለነበረው ብቸኛ አማራጭ (ጉልበትን ብቻ መጠቀም) ሊኖር የሚችለው ወይንም ይዞ ለሚመጣው ጣጣ በዚያው ልክ አልተዘጋጀበትም ነበር፡፡

## III. የግንቦቱ ምርጫ: የተቃዋሚዎች አመለንካትን ዝግጅት (1)

(ሀ) የግንቦቱ ምርጫ ከዚህ በፊት ከነበሩት ምርጫዎች ይለያል ወይንስ ያው እንደቀድሞዎቹ ይሆናል በሚለው ላይ በተቃዋሚዎች አካባቢ የነበረው አመለንካትና የህዝቡ ሥሜት

- በዚህ ላይ በቅንጅቱ አካባቢ የተለየ ይሆናል በሚል ለምርጫው በሙሉ ልብ መዘጋጅት ይገባል የሚለው አመለካከት የጊዜያዊ ስልት ጉዳይ ሳይሆን መሰረታዊ አመለካከት ነበር፡፡ በህብረቱ አከባቢ ግን ለምርጫው ትንሽ ሳምንታት እስከሚቀረው ድረስ በምርጫው አለመሣተፍ እንደ አንድ አማራጭ ተይዞ ነበር፡፡ ይህም የሁለቱ ድርጅቶች አወቃቀርና (በህብረቱ በኩል የውጭ ድርጅቶች ተፅእኖ ወይም (influence) አፈጣጠር የፈጠረው ነው፡፡
- በመጀመሪያው ላይ በህዝቡም በኩል ምርጫውን ከምር የመውሰድ ሥሜት አልነበረም

(ለ) ምን አይነት አደረጃጀት የተሻለ ውጤት ይሰጣል?

(ለ-1) በአገር ውስጥ የሚገኙ የተቃዋሚ ድርጅቶችን አሰባስቦ ለምርጫው ማዘጋጀትና ምርጫውን ጥሩ ፉክክር እንዲኖረው ለማድረግ የተደረጉ ጥረቶች በአገር ውስጥ

(የአራቱ ሽማግሌዎች ጥረት ለምን ከሸፈ? የህብረቱ መቋቋም በአሜሪካ፣ የመኢዴፓ የኢዴፓ ከህብረቱ መውጣት)

(ለ-2) ቀስተደመናን ለማቋቋም የተደረጉ ውይይቶችና የተደረሰባቸው አጠቃላይ ሥምምነቶች

- ስለምርጫው ጠቀሜታ (አገሪቱን ከቀውስ ለማዳን) የነበረን ግንዛቤ
- ምርጫው ውጤት እንዲያመጣ የተቃዋሚ ፓርቲዎች በአንድነት መስራት አስፈላጊነት
- ከዚህ በፊት አብሮ ለመስራት የነበራቸውን ችግር ምክንያት መለየትና ለችግሮቹ መልስ መስጠት
- ከብሄር ፖለቲከ የወጣ ዘመናዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሁም አገራዊ ራዕይ ማስፈለጉና ይህንን በቀላሉና ለህዝቡ በሚገባ መልኩ የማዘጋጀትን አስፈላጊነት
- ከፖለቲከ የራቁ የአገሪቱ ልሂቃንን ፖለቲካው ውስጥ በዚህ ራዕይ አማካኝነት የማሰባሰብ አስፈላጊነት
- ለዚህ ራዕይ የሚያስፈልገው አደረጃጀትና ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚገጥሙ ፈተናዎች (ህብረ-ብሄራዊ ድርጅቶችን ማሰባሰብና ፖለቲካን ከብሄር ወደ አስተሳሰብ ማዞር)

(ለ-3) ቅንጅቱን ለመፍጠር ቀስተደመና የጀመረው እንቅስቃሴና የገጠሙ ችግሮች

- ቀስተደመና (መስራቾች) ሁሉንም ህብረብሄራዊ ድርጅቶች በግል ማነጋገርና በመሰረታዊ ነጥቦች ላይ ማስማማት ብዙ ችግር አልነበረም:: አብሮ መታገል ለውጤት አስፈላጊ መሆኑን ሁሉም አምኖበታል፡ እርስ በእርስ አለመወዳደርን አስፈላጊነት ያልተቀበለ አልነበረም
- የመሰብሰቡ መስፈርቶች፡ ሕብረብሄራዊነት፣ በምርጫው መሳተፍ
- ኢድህ በህብረቱ ውስጥ ስለገባ ቅንጅቱን መቀላቀል አለመፈለጉ፡ መኢዴፓ ላይ የኢዴአፓ-መድህን (በተለይ ልደቱ) ተቃውሞና እነሱ ከገቡበት እንደማይሳተፍ መግለፁ፣ ያቀረባቸው ዝርዝር ተቃውሞዎች በጊዜው ተቀባይነት ማግኘታቸው
- አራቱ ድርጅቶች ቅንጅትን ለመመስረት በመሰረተ ሀሳብ ደረጃ መስማማታቸው::
- በድርጅቱ አወቃቀርና በአመራሩ ውክልና ላይ የተነሱ ጥያቄዎች
- ሁሉም ድርጅት በእኩልነት ይወከል ወይንስ ለአንጋፋዎቹ ድርጅቶች የበለጠ ውክልና ይሰጥ?
- በመኢአድና በኢዴአፓ-መድህን መሀል ያለ ጥርጣሬ የድርጅቱ ሊቀመንበር ማን ይሁን? እስከመቼ?

- በአንጋፋዎቹ ድርጅቶች ውስጥ ያለው (የነበረው) ድርጅታዊ ባህል፡ አሰራር፡ አስተሳሰብ አዲሱን ድርጅት ከሚፈጥረው ራዕይና አደረጃጀት ጋር ያመጣቸው አለመጣጣሞች
- ግለሰባዊ (Personalized) አሰራር፡ ጥቂት ግለሰቦች በድርጅቶቹ ላይ ያላቸው ጥንካሬ ተፅእኖ፣ የተዳከመ የውስጥ ድርጅት ዴሞክራሲ
- ከድርጅቶቹ ታሪክና ከልሂቁ መሸሽ የመጣ የተዳከመ የፖለቲካ ትንተና ችሎታ ያለው የሰው ሀይል ስብስብ (የብዙ ሰው ጠንካራ ፍላጎት እንጂ ጠንካራ ችሎታ አለመኖር)
- የውስጥ ድርጅት ክፍትነትን ማጣት ያመጣው ሥር የሰደደ የወሬና የሀሜት ባሕል

(ሐ) ቅንጅት እንደተፈጠረ ወደ ምርጫው መግባቱ የፈጠረው የጊዜ መጣበብ፣ ዝርዝር መዋቅሮችን ሰርቶ ተግባራዊ ማድረግ አለመቻል በዚህም ምክንያት ብዙውን ነገር ዝም ብሎ በመታመን እንጂ መዋቅራዊ መሠረት በመስጠት አለመስራት

- በፊት ለፊት የማይወጡ ግን ስር የሰደዱ ግለሰባዊና ግል-ድርጅታዊ ስሜቶች በቂና መዋቅራዊ መሰረት በመስጠት አለመስጠት፡ ከህጋዊና መዋቅራዊ እንዲሁም ተግባራዊ መፍትሔ ይልቅ ባብዛኛው ለሞራላዊ ግፊቶች ትኩረት መስጠት

(ሐ.1) የመጀመሪያው ከፍተኛ ቀውስ በቅንጅት ተወዳዳሪዎች በማቅረብ ረገድ የገጠሙ ፈተናዎች

- ተወዳዳሪዎች በምን መስፈርት ይቅረቡ (ትምህርት ምን ያለው?)
- የተስማማንበት መስፈርት ከድርጅት ታሪክ ጋር በቅጡ ተገናዝበዋል? ይህ የፈጠረው መዘበራረቅ በተለይ በመኢአድ
- ብዙ ተወዳዳሪ ለማግኘት የነበረው ቅጥ ያጣ ውድድር በሁለቱ ድርጅቶች መካከል ተቀብሮ የነበረውን የቀድሞ ልዩነት ሁሉ በግልፅ ማውጣቱ:: የልደቱን ብልጥነት መኢአዶች መቋቋም አልቻሉም
- የቅንጅቱ ለመፍረስ መቃረብና የመጨረሻዎቹ የማስማማት ስራዎች
    - መኢአድ በመጨረሻ ሰአት ብቻውን ሊመዘገብ መወሰኑ
    - ሌሊት ያሳደሩት ድርድሮች (ሌሎች ድርጅቶች በመኢአድ ላይ የነበራቸው ቅሬታ)
    - ልደቱ ተገባልኝ የሚለው ተስፋ (promise) - indicative of the then tension)

(መ) በቅንጅትና በህብረት መሐከል የነበረው የመጀመሪያዎቹ የሽኩቻ ሂደቶች

(መ-1) የብሔር ድርጅቶች "የትምክህተኞችና ቀኞች" ክስ

(መ-2) ቅንጅት ከብሄር ድርጅቶች ጋር አሁንም አብሮ ለመስራት ፍላጎት አለው የሚለው አቋም

(መ-3) የህብረቱ የውጭ ተፅእኖና የአገር ውስጥ አመራሮች አመለካከትና በውስጣቸው የነበረው ልዩነት (በበየነና በመራራ በተለይ ኢሕአዴግን በተመለከተ- ልደቱና በየነ)

(መ.4) በሁለቱ ድርጅቶች መሀከል እያደር እያደገ የመጣው የአብሮ መስራት ፍላጎት:: በተለይ ከመራራ ሊቀመንበርነት በኋላ

(ሠ) ሁሉም ተቃዋሚ አንድ አይነት ራዕይ ነበረው? ለአንድ አላማ ነበር የሚታገለው

(ሠ-1) ለዴሞክራሲ የነበረው ወገንተኛነት ታክቲከዊ ወይንስ ሥር የሰደደ አላማ

(ሠ-2) ልዩነቶች ምን ያህሉ የአላማ? ምን ያህሉ ግለሰባዊ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ግን ግልፅ ያልወጣ?

(ሠ-3) ልዩነቶችን አቻችሎ አብሮ ለመስራት ዴሞክራሲን የሚጠቅም ወይንስ መርህ አልባ የሚያደርግ

## IV. የግንቦቱ ምርጫና የቅንጅት የምርጫ ዘመቻ እስትራተጂ (2)

- በግልፅ የተፃፈ እስትራተጂ ባይኖርም የምርጫ ዘመቻ ኮሚቴው የሚሰራበት አጠቃላይ አቅጣጫ ነበረው

(ሀ) በምርጫ ለውጥ የመጣል? ሕዝቡን በምርጫ ለውጥ ይመጣል ብሎ እንዲያምን የሚደረግ የመጀመሪያ ትግል ይህ እንዲሆን ሁለት የተያያዙ ስነልቦናዊ ጥያቄዎችን በመጀመሪያው ምርጫ ዘመቻ ወቅት አጠንክሮ መስራት እንደሚያስፈልግ እነኝህም

(ሀ-1) ማህበረሰቡን ከፍርሀትና በተለይም ከመንግሥት ፍርሀት ማላቀቅ ለዚህ ግን የመንግስትን ምንነትና የነፃነት አስፈላጊነት ላይ ሰፊ ትምህርት መስጠት

- በዚህ ላይ የሬድዮና የቴሌቪዥን ክርክሮች በጣም ረድተዋል (ለካ መንግስትን መስደብ ይቻላል)::

(ሀ-2) በራስ የመተማመንና እኔ የማደርገው ነገር (ድምፅ መስጠጠ) ፋይዳ አለው የሚል እምነት እንዲኖረው ማድረግ

- በዚህ ላይ ሥለ ድምፅ አሰጣጡ፣ ድምፅ ሲሰጥ የህሊና ጉዳይ እንደሆነ ማጭበርበር እንደማይቻል (በተለይ ሕዝቡ ከጠበቀ) በሰፊው ማስተማር፡፡

(ለ) ለህዝብ የሚቀርበው መልእክት ወጥ እንዲሆንና ለህዝቡ በቀላሉ እንዲገባ ማድረግ

(ለ-1) አንድ ድርጅት አንድ አርማ ሁለት ጣት እንዴት ተመረጠ የቅንጅት እድል

(ለ-2) አንድ አይነት መልእክትና በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ ማተኮር

- የነፃነትና የዴሞክራሲ አስፈላጊነት
- የአገር አንድነት፡ የብሄሮችን እንድነትና ፍቅር ማጉላት
- የኢኮኖሚ ችግሮች ለህዝቡ በሚገባው መሰረት
- የፍቅርና መተሳሰብ ላይ ማተኮር (ከጥላቻ ማራቅ) — (**Positive message**)

(ሐ) የሚዲያ አጠቃቀም ሂደት

- የሚዲያ እስትራተጂ አስፈላጊነት ግን ከመዘጋጀቱ በፊት በሁኔታዎች መቀደም
- የመጀመሪያዎቹ አውንታዊ መልእክቶች
- የኢህአዴግ የኢንተርሀምዌይ ክስና የቅንጅት የሚዲያ እስትራተጂ በተወሰነ ደረጃ መቀየር (**From Positive message to negative companign**)

(መ) የቅንጅት የምርጫ ዘመቻ አደረጃጀትና ችግሮች (ሚዲያ፣ መድረክ፣ ሥነፅሁፍ ኮሚቴዎች)

- ድርጅቶቹን ለምርጫ ዘመቻው በሚጠቅም መንገድ ማቀናጀት (ከማእከላዊ እስከ ወረዳ ድረስ የተለያዩትን ድርጅቶች የማቀናጀት ሂደትና የገጠመው ፈተና (አሁንም የግል ድርጅት ፍላጎቶች አልሞቱም)
- የምርጫ ዘመቻውን በምርጫ ክልል ደረጃ ማደራጀትና ይህ ከቀድሞው የድርጅት አወቃቀር ጋር የፈጠረው ግጭት
- ከማእከል ወደክልል ለቅስቀሳ ሲኬድ የተነሱ ጥያቄዎች (በምን መስፈርት?) የት የት ይካሄድ? ማን ይሂድ? (የሰው እጥረት) የምረጡኝ እንቅስቃሴው ቦታ (አዳራሽ? መስክ ላይ? በየመንገዱ)

(ሠ) የቅንጅት የፋይናንስ ችግር:-

(ሠ-1) በቅንጅት ሥር የተሰባሰቡ ድርጅቶች ከቅንጅት መመስረት በፊት ምን ያህል ገንዘብ ነበራቸው? ምን ያህል ገንዘብ አለን ይላሉ? ምን ያህል ወጪ አላቸው?

- የለንም በስተቀር ይህ መረጃ በየድርጅቱ በውስጥ የተያዘ ነበር

(ሠ-2) የድርጅቶቹ የገንዘብ ማሰባሰብ ታሪክ በአብዛኛው ውጪ በሚገኘው ኢትዮጵያዊ ላይ ያተኮረ መሆኑ፡፡ ከአገር ውስጥ ምንጮች (በተለይ ከብዙሀኑ) ለመጠቀም ብዙ ጥረት አልነበረም

(ሠ-3) የመጀመሪያው እርሾ ከሶስቱ ድርጅቶች የተደረገ መዋጮ (ለቢሮ … ወዘተ)

(ሠ-4) ከውጭ የሚሰበሰብ ገንዘብ በቅንጅቱ ወይንስ በግል ድርጅቶቹ? የአሜሪካ ገንዘብ ማሰባሰብ ያስነሳው ችግርና የቀረበው መፍትሄ ከቅንጅቱ ሀሳብ ውጭ ሌሎች በግልፅ ያልወጡ ስሜቶች በውጭ አገር ነበሩ?

(ሠ-5 በአጠቃላይ ምን ያህል ገንዘብ ተሰበሰበ? ገንዘቡ በምን ላይ ዋለ?

(ሠ-6) ቀድሞ የነበረው የገንዘብ አወጣጥ ባህልና አዲስ የተመሰረተው አሰራር ቀልጣፋ አሰራር ወይንስ አስፈላጊ ቁጥጥር?

(ረ) ቅንጅት ከምርጫው ምን ይጠብቃል?

(ረ-1) የምርጫ ዘመቻውን ካለብን የተለያዩ እጥረቶች አንፃር በቦታ ደረጃ ለመወሰን (Focus) በምርጫው ያለንን የማሸነፍ እድል ማስላት አስፈላጊነት

(ረ-2) ካልተማከለ የግምት ውይይት ትንሽ የታሰበበት ዝግጅት፡፡ የቀረቡት አማራጭ ይሆናሉ ተብዬዎች (alternative scenarios) የልደቱና የሀይሉ ሻውል ግምቶች እና የቅንጅት አቋም

(ረ-3) ልዩነቶቹ ዝም ብለው የተስፋ ግምቶች ወይንስ የየድርጅቶቹን አጠቃላይ አመለካከትና አደረጃጀት የሚያሳይ መሰረታዊ ልዩነት? ኢሕአዴግን ማሸነፍ ይቻላል አይቻልም? ለምን?

(ረ-4) ስለምርጫው ውጤት የነበረው ግምት ግን እያደር የምርጫው ሁኔታ እየተሟሟቀ ሲሄድ እየተቀየረ ይሄድ የነበረ እንጂ ከመጀመሪያውም ወጥ የነበረ አልነበረም፡፡

## V. ከምርጫው ዘመቻ መጀመር እስከ ግንቦቱ ምርጫ (ከጥር-ግንቦት)

1. የመጀመሪያዎቹ ሁለት ወራት

(ሀ) የፀረ-ፍርሀትና ፀረ-ተስፋ መቁረጥ ቅስቀሳው በተወሰነ ደረጃ መስራት መጀመሩ:: በመጀመሪያው የተመዘገቡ ጥሪ የነበረው የመራጮች ምዝገባ ዝቅተኛነት:: ቅንጅት የመጀመሪያዎቹን ሁለት ሣምንታት ግድም ህዝቡ እንዲመዘገብ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማድረጉ (በሚዲያም ሆነ በየመንገዱ)

(ለ) በነኝህ እንቅስቃሴዎች (የመጀመሪያዎቹን ክርክሮች ጨምሮ) በተወሰነ ደረጃ የህዝቡ ተስፋ መመለስ መጀመሩ:: ብዙ አዲስ አባላት መመዝገብ መጀመራቸው፣ ከዚህ በፊት ተኝቶ ከነበረው የህዝብ ክፍል (የተማረ፣ መሀከለኛ ገቢ፣ ወጣት ... ወዘተ) ከፍተኛ እንቅስቃሴ መታየት መጀመሩ

(ሐ) የተለያዩ ግለሰቦችም ሆኑ በተለይ የሲቪክ ማህበረሰብ አባላት በየራሳቸው ተነሳሽነት የሚወስዷቸው እንቅስቃሴዎች በአጠቃላይ የህዝቡን ሙሉ ስሜት ወደ ምርጫው መውሰድ

(መ) ከአልመዘገብም (ምንም ለውጥ አያመጣም) ባይነት እስከ ባለመመዝገብ መቆጨት

(ሠ) የሬድዮና የቴሌቪዥን ክርክሮችና ፋይዳቸው

- የመጀመሪያው የኢንተር አፍሪካ ፕሮግራምና የቅንጅቱ ዝግጅት (እነማን ይከራከሩ በሚል በእኔና በልደቱ የተነሳው ክርክር፤ ከየፓርቲው ይውጣጣ ወይንስ በብቃት ብቻ ይሁን? ለዝግጅት የነበረው የጊዜ እጥረት::
- የገጠር ልማት ክርክርና የኢህአዴግ የተጨማሪ ክርክር ጥያቄና ያልተሳካበት ምክንያት
- ከየክርክሩ በኋላ የሚነሱ የኢህአዴግ ጥያቄዎች (የክርክር ርዕሶች ምን ይሁኑ?) አዳራሽ ውስጥ ማን ይግባ? የጭብጨባ ጉዳይ … ወዘተ)
- በክርክሩና በምርጫው ጉዳይ ዙሪያ ከበረከት ጋር የነበሩን ውይይቶች

## 2. የኢህአዴግና የቅንጅት የተለያዩ የምርጫ ዘመቻ አካሔዶች

(ሀ) ኢሕአዴግ ጠንካራ ድርጅትና ጠንካራ ፋይናንስ - ስለዚህም የተሻለ የተደራጀና የበለጠ የተዘጋጀ (More organized and controlled) ዘመቻ ግን ካጣ ብዙ የሚያጣ::

(ለ) ቅንጅት ደካማ ድርጅትና ደካማ ፋይናንስ፣ በቂ ዝግጅት ያልነበረው:: ስለዚህም የበለጠ ዘብራቃ፣ ወዲያው ወዲያው ውሳኔዎች የሚሰጥበት ስለሆነም በጣም

ከየጊዜው ሁኔታ ጋር ተለዋዋጭ (highly disorganized but feasible to adapt to new coalities)

(ሐ) ኢሕአዴግ በተለይ በክልል ከተሞች ምንም አይነት የዘመቻ ስብሰባዎች (campaign rallies) አላደረገም፡፡ ውስጥ ለውስጥ በሚደረጉ ድርጅታዊ ስራዎች ነበር የተማመነው፡፡ የኢህአዴግ ተወዳዳሪዎች ከህዝቡ ጋር ግንኙነት አልነበራቸውም፡፡ (Impersonal compain ralying on the organization and the media)

(መ) የቅንጅት ዘመቻ በጣም (personalized) ነበር፡፡ በዙ የህዝብ ስብሰባዎች በየክልሉ፡፡ ብዙ የየወረዳ ተነሳሽነት (local initiative)፡፡ በዚህም ምክንያት በየስብሰባዎቹ የሚገኘው የህዝብ ብዛት በየጊዜው እየጨመረ ከአዳራሽ ወደ መስክ ከዚያም በየመንገዱ በማድረግ አለን ለማለት ተችሎ ነበር፡፡

- በየቦታው የነበረው የህዝብ ጥሪን ማዳረስ አልተቻለም ነበር

## 3. የህዝባዊ ስብሰባዎች መልእክትና የኢህአዴግ ሽብር የመጀመሪያ ደረጃ

(ሀ) በቅንጅት በኩል ወጥ መልእክቶች ባይኖሩም (በተቻለ መጠን የየቦታውን ሁኔታ የሚመለከቱ ጉዳዮች እንዲነሱ ፍላጎት ነበር) ግን የተወሰኑ ወጥ መልእክቶች በቀላል ሁኔታ ይቀርቡ ነበር (ዴሞክራሲ፣ ኤርትራ፣ ድህነት፣ … ወዘተ)

(ለ) የኢህአዴግ የመጀመሪያዎቹ ከጭንቅ የመጡ ክሶች (ታክስ አትክፈሉ ትላላችሁ) የዘር ቅስቀሳ (በረከትና ልደቱ - ኤርትራዊነት) ይህ በፍጹም የቅንጅቱ አቋም አይደለም፡፡ የኢህአዴግ የሽብር ምልክቶች ይመስላሉ (በቅንጅት ስብሰባዎች በሚገኘው የሰው ብዛት)

(ሐ) በቅንጅት በኩል በተቻለ መጠን መንግሥት (provoked) እንዳይሆን ጥንቃቄ ይወሰድ የሚል አጠቃላይ ግንዛቤ ነበር (ገበያ ዘመቻ እንዳይካሄድ፣ በሚነገሩት ነገሮች ጥንቃቄ ወዘተ)

## (4) የመጨረሻው አንድ ወር (የኢህአዴግ ሽብር እያየለ መምጣት)

(ሀ) ኢህአዴግ በክርክሮች የደረሰበት ሽንፈትና የኢህአዴግ የውስጥ ድክመት መጋለጥ

- ኢህአዴግ ለክርክሮች በቂ ዝግጅት (ተከራካሪዎቹ) አድርገው ነበር?

- ዴሞክራሲና የህብረተሰብ ክፍሎች አለማስቀየም (በክርክሩ ላይ ስለ ሲቪክ ማህበረሰብ፣ ስለሚዲያ የተባሉ ነገሮች የፈጠሩት ችግር)
- የህዝብ ፍላጎት በክርክሮቹ ላይ፡ በኢህአዴግ የተሰሩ አንዳንድ የታክቲክ ስህተቶች ህዝብ ስብሰባ እንዳይገባ መከልከል፣ ... ወዘተ አኩራፊና ተሸናፊ አስመሰለው)
- የኢህአዴግ ትላልቅ ካድሬዎች መቅረብ ለኢህአዴግ ጥሩ ወይንስ መጥፎ እስትራተጂ አማራጭስ ነበረውን? ለተቃዋሚዎች የማይሸነፉበት መድረክ ነበር (በክርክሩ እንኳን ቢሸነፉ የሚከራከሩት ለብዙ አመታት ሚኒስቴር ከነበሩ ሰዎች ጋር መሆኑ በህዝቡ ዘንድ ማስተዛዘኛ ያስገኝላቸዋል)

(ለ) የመስክ ስብሰባዎችና በተለይ በክልሎች የህዝቡ ከፍተኛ ፍላጎትና ለተቃውሞው የሚሰጠው ድጋፍ በየክልሉ ባሉ ካድሬዎች የፈጠረው መደናገጥና በአንዳንድ ክልሎች የተወሰዱ የተናጠል የሀይል እርምጃዎች (ወላይታ፣ ኦሮሚያ፣ አንዳንድ የአማራ ወረዳዎች)

(ሐ) ምርጫውን ለመታዘብ የውጭ ድርጅቶችና በተለይም የአገር ውስጥ የሲቪክ ማህበራትን እንዳይታዘቡ መከልከል የኢህአዴግን መደናገር እያጎላ መምጣቱን ማሳየቱ -በምን መሰረት የውጭ ታዛቢዎች ከለከሉ? (CDI? Norway)

  - በምን መሰረት የአገር ውስጥ ታዛቢዎችን ከለከሉ? የምርጫ ቦርድ ትዝብት ላይ መውደቅ

## (5) ሚያዚያ 29 እና 30: እውነተኛ ሽብርና መተራመስ በኢህአዴግ ጎራ

(ሀ) የቅንጅት የሚያዚያ 30 አላማና ዝግጅት

- የታሰበው ገና የምርጫ ዘመቻው ሲጀመር እንደ አወንታዊ የምርጫ ማጠቃለያ የመዝናኛ ፕሮግራም ተደርጎ ነበር፡፡ ሁለት ሳምንት እስኪቀረው ምንም ዝግጅት አልነበረም
- የኢህአዴግ የሚያዚያ 29 ፕሮግራም ግን ቀድሞ የታሰበበት አልነበረም
- ሚያዚያ 29 ሰልፍ፡ ደንበኛ የደርግ አይነት በመንግስት የተዘጋጀ በማታለልና በማስፈራራት ላይ የተመሰረተ ሰልፍ
- የአላሙዲ ለኢህአዴግ ግልፅ ድጋፍ ለቅንጅቱ ያልተጠበቀ ቦነስ (ከአበሻ ስነልቦና አንፃር)
- ሚያዚያ 29 ለሚያዝያ 30 የሰጠው ድጋፍ (ሰውን እልህ ውስጥ ማስገባት)

- በቅንጅት በኩል የተደረገው በጣም አነስተኛ ዝግጅት (በጣም አነስተኛ ያልተሣካ የታማኝ ቪዲዮ)
- ሚያዚያ 30 ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ልዩ ቀን
- የነበረው የህዝብ ብዛትና የሰው አይነት (እራሱ ባዘጋጀው መፈክር ያለምንም ድርጅት ምናልባት በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያውና ትልቁ በፈቃደኝነት የተደረገ ትዕይንተ ሕዝብ
- የሰው ጨዋነትና የደስታ ሥሜት (a feative atmosphere)
- አዲስ አበባ ወዴት እንደሚሄድ ግልፅ ሆነ፣ ትኩሳት ወደ ክልሎች ተሸጋገረ (ጎንደር፣ባህርዳር፣አዋሳ፣ደብረ ዘይት፣ … ወዘተ)

(ለ) ሚያዚያ 30 እና የኢህአዴግ እውነተኛ ሽብር

- ኢህአዴግ በመጥፎ ሁኔታ ከእንቅልፉ ነቃ በነፃ ምርጫ የመሸነፍ ዕድል ሊኖር እንደሚችል ይታያቸው ጀመር
- የኢህአዴግ የፕሮፖጋንዳ መልስ ለሚያዚያ 30 (የበድሩ ንግግር ላይ ማተኮር;
- የአርከበና የአዲስ አበባ መስተዳድር የድረሱልኝ ጩኸት (ግብር ምሬአለሁ፡ የትራፊክ ቅጣት አንስቼሰለሁ፡ 300000 ቤት ልሰራ ነው ተመዝገቡ … ወዘተ የመሽበር አስቂኝ ድራማ
- የሁሙስ ግንቦት 4 የመጨረሻ የምርጫ ቅስቀሳ (ስብሰባ ማእከል) እና የኢህአዴግ የሻማ ማብራት ፕሮግራም ቀውስ
- በክልል የአፈናው እንቅስቃሴ በእጅጉ ተጠናከረ፤ የክልል ህዝባዊ ስብሰባዎች ችግር ይገጠማቸው ጀመር
- የአለም አቀፉ ማህበረሰብ ስለምርጫው ውጤት የነበራቸው ግምት (ውይይት የአውሮፓና የአሜሪካ)
- በገጠር አካባቢዎች የፓርቲ የምርጫ ታዛቢዎች (ይሆናሉ ተብለው የሚታሰቡት) መታሰርና መንገላታት ጀመሩ፡፡ ታዛቢዎች መመልመል አስቸጋሪ መሆን ጀመረ፡፡ ተቃዋሚ ድርጅቶች የታዛቢዎችን ሥም ለምርጫ ቦርድ እስከመጨረሻው ሰዓት አለመስጠት (እስከ ሀሙስ ግንቦት 4 ድረስ)፤ ግንቦት 4 እና 5 ስም መስጠት ሲጀመር በተለያዩ ቦታዎች እልፍ ታዛቢዎች በስፋት መታሰር ጀመሩ፡፡

- የተቃዋሚዎች የኢዴአፓ ጋዜጣዊ መግለጫ በሆቴል ዴ ሊኦፖል (ሁሉም የተሳተፉበት)
- የመጨረሻው የኡኡታ ጋዜጣዊ መግለጫ ግንቦት 6 በምርጫ ታዛቢዎች መታሰር ዙሪያ
- የመጨረሻው ነፃ የቴሌቪዥን ወይይት (አቶ መለስ፣ መራራና በየነ፣ እኔና ልደቱ)

(ሐ) የምርጫው እለት (ግንቦት 7)

(ሐ-1) ምርጫ በአዲስ አበባ

- ህዝቡ በሌሊት ሰልፍ ጀመረ
- የምርጫ ጣቢያዎች ብዙ ቦታ በጊዜ አልተጀመሩም በጣም ረጅም ሰልፎች ተከሰቱ
- የምርጫ ቦርድ በቶሎ የምርጫ ሰአቱን አራዘመው - አወንታዊ እርምጃ
- በየምርጫ ጣቢያው ችግሮች ለመፍታት የተደረጉ ጥረቶች (በወረዳ 21/22 የተገው ምልክት የተገኘባቸው መምረጫ ወረቀቶችና ያቀረብናቸው መፍትሔዎች
- የህዝቡ (exitement) አልሰረቅም በሚል የሚቀርቡ ብዙ የተሳሳቱ ሪፖርቶች፣ የታዛቢዎች የሚገርም የንቃት ተሳትፎ:: (የአገር ውስጥም የውጭም)

(ሐ-2) የምርጫው እለት በክልሎች

- የሚቀርቡ የተለያዩ አወንታዊም አሉታዊም ሪፖርቶች ከድርጅት ሰዎች (አፋር፣ ምስራቅ ጎጃም፣ ደቡብ ጎንደር)

(ሐ-3) ምርጫውን በሚመለከት የሊቀመንበሩ የተቻኮለ የBBC መግለጫ ከመጥፎ የክልል ሪፖርቶች በመነሳት

(ሐ-4) የጠቅላይ ሚኒስትሩ የአሁድ ማታ መግለጫና የፈጠረው ስሜት (ችግር ሊኖር ነው?) የአስቸከይ ጊዜ አዋጅ

(መ) የክፍል ሁለት መደምደሚያ

## ክፍል: III ከምርጫው በኋላ እስከ እስርቤት: የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ወዴት

(ሀ) የምርጫው ማግስት የነበረው ሁኔታ

- እሁድ ከሌሊቱ 10 ሰዓት ገደማ ከአዲስ አበባ ውስጥ 15ቱን ወረዳ በሙሉ በሰፊ ልዩነት ማሸነፋችንን ከታዛቢዎቻችን ከሚደርሰን ሪፖርት እርግጠኛ ሆንን፡፡ ቀሪዎቹ ገና ሙሉ ለሙሉ ተቆጥረው ያላለቁ ነበር (ይህን እንዳወቅን ከአንዳርጋቸው ጋር እቤት ሄድን)
- ሰኞ ቀን እሁድ ቆጠራ ተደርጎ ያለቀባቸው የክልል ወረዳዎች ሪፖርት መድረስ ጀመረ ሪፖርቱም በጣም ጥሩ ነበር ለተቃዋሚዎች፡፡ እስከ ሰኞ ማታ ቆጠራው አልቋል ተብሎ ሪፖርት በደረሰባቸው ቦታዎች ተቃዋሚዎች በሰፊ ልዩነት የመራሉ፡፡
- የሰኞ በ10 ሰዓት ጋዜጣዊ መግለጫ አዲስ አበባን (17 ወረዳዎች ማሸነፋችንን የሚገልጽ
- የሰኞ ማታ የኢህአዴግ መግለጫ የኢህአዴግ ኩዴታ (coup de etat)
- ከአንዳንድ ቦታ የታዛቢዎችን መባረር ሪፖርቶች (ቆጠራ ከመጠናቀቁ በፊት)

(ለ) ከማክሰኞ ግንቦት 8 እስከ ግንቦት 29

- ከክልል የሚመጡ ሪፖርቶች መቆም (በታዛቢዎቻችን በኩል)
- በክልል በገጠር ወረዳዎች ከፍተኛ ማጭበርበር እየተደረገ እንደሆነ (ኮሮጆ መገልበጥና መቀየር፡ ... ) ሰፊ ሪፖርቶች መቅረብ ጀመረ
- በቅንጅት በኩል ምርጫው በግልጽ እየተጭበረበረ እንደሆነ የጋራ ግንዛቤ ላይ ተደረሰ ከህብረትና ከሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር በተደረጉ ውይይቶች የመጭበርበሩ ሁኔታ በሰፊው እንደሆነና ይህንንም መፍጹም እንደማንቀበለውና በጋራ መታገል እንዳለብን
- መንግስት አፈና ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ገባበት፡፡ የደህንነት ወከባ፡፡
- የተጭበረበረው በአብዛኛው የውጭ ታዛቢዎች በሌሉበት መሆኑ
- በቅንጅቱ ውስጥ የተፈጠረው ስሜት፡ ከከፍተኛ ደስታ ወደ ቁጭትና ንዴት
- ምንም እንኳን ከኛ ታዛቢዎች ምንም ሪፖርተ መስማት ብናቆምም ኢህአዴግ በምርጫ ቦርድ በኩል በየእለቱ የአሸነፍኩ ጊዜያዊ ውጤት መግለጫውን ቀጥሏል፡ ይህም በህዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ቁጣን ይቀሰቅሳል፡፡ ማታ በቴሌቪዥን ኢሕአዴግ አሸነፈ የተባለበት ቦታ በነጋታው ከህዝቡ ቢሮአችን እየተደወለ የሚቀርበው የተጭበረበርን ኡኡታ

- የቅንጅቱ እለታዊ ስራ ጋዜጣዊ መግለጫ መስጠት ሆነ። በዚህ ጊዜ የነበረው የልደቱ አክራሪ አቋምና የቅንጅቱ ማእከላዊ ም/ቤት የማለስለስ ሙከራ (ኢሕአዴግ እንዳይደነብር እናድርገው።)
- ከማክሰኞ በኋላ በተፈጠረው ሁኔታ የምርጫው ውጤት ምን እንደሆነ በእርግጠኝነት ማንም መናገር አልቻለም
- የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ውጤት የናሙና ጥናትና የዲፕሎማሲያዊው ማህበረሰብ መደናገጥ (ያልጠበቁት ውጤት መሆኑ)
- የአውሮፓ ህብረትና የካርተር ማእከል ስለምርጫ ቆጠራው ያቀረቡት ሪፖርት፡ ከአገር ውስጥ ታዛቢዎች የሚቀርቡ ሪፖርቶች

(ሐ) ቅንጅቱ ጉዳዩን በሰፊውና እስትራተጂክዊ በሆነ መልኩ አይቶ አቋም መውሰድ አለበት

- ከእለት ተእለት መግለጫ ማውጣት ወደ እስትራተጂካዊ አስተሳሰብ የመሄድ ችግር
- ሊሆን የሚችል ሁኔታ ትንታኔ (Scenario Analysis) አስፈላጊነት
- ኢሕአዴግ ምን እያሰበ ነው ምን ድረስ ይሄዳል ቅንጅቱስ እስከምን ድረስ ይጋፋል ሕዝቡስ ምን ድረስ ይሄዳል? በጊዜው የነበሩ አንዳንድ ውይይቶች
- የቅንጅቱ የ"ትዕግስት" ጥሪና የምርጫው በገለልተኛ ወገን ይጣራ ጥያቄ (የመጀመሪያ አቋም)
- ይህ ከልሆነ ሊሆን የሚችለውን የሰላማዊ ትግል ጥሪ ማስታወቅ ወይንስ አለማስታወቅ (ልደቱ VS እኔ)
- ከምርጫ ማጣራቱ ጥያቄ በተጨማሪ የሚዲያ አጠቃቀምና የዴሞክራሲያዊ ሒደቱ መቀጠል ጥያቄ
- የህዝቡ ግፊት እያየለ መሔድና የቅንጅቱ የ"ትዕግስት" ጉዞ እያደር ደካማ መምሰል
- በዩኒቨርሲቲ አካባቢ የሚካሄዱ የተናጠል እንቅስቀሴዎችና የቅንጅቱ አቋም (በመጀመሪያ ለውይይት ከመጡ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች የሰጠሁት መልስ፡- ወደ ግጭት የሚወስድ እርምጃ መወሰድ የለበትም) በተለይ መንግስት ለግጭት ሰበብ እየፈለገ ስለሚመስል መሳሪያ መሆን አይገባም
- ግንቦት 29 እና 30 የተማሪዎች እንቅስቃሴና በቅንጅቱ ውስጥ የነበረው የተዘበራረቀ ስሜት (በአንድ በኩል ህዝቡ ድምጹ እንዲከበርለት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ መደገፍ በሌላ በኩል ኢህአዴግ ይህን ለሰፊ አፈና የሚያደርገውን እንቅስቃሴ እርምጃ ምክንያት ላለመሆን ስጋት)

- ግንቦት 30 የተበተነው የሥራ ማቆም አድማ ጥሪና የቅንጅቱ አቋም
- ኢህአዴግ የቅንጅቱን የሥራ ማቆም ጥሪ የሚቃወም መግለጫ አላወጣም ማለቱ ኢህአዴግ አገሪቱን ወዴት ሊወስዳት እንደሚፈልግ ያመለክታል?
- በከተማው የሚበተኑ ወረቀቶች ማን ነው የሚበትናቸው? ለምን የመንግስት ደህንነት መስሪያ ቤት ምን ያህል እጅ አለበት? ወይንስ ሌሎች "አክራሪ" ሀይሎች በስተጀርባ እየተደራጁ ነው? ይህስ ከሆነ አገሪቱ በኢህአዴግና በነኝህ ሀይሎች ግፊት ወዴት እየሄደች ነው? በዚህ ሁኔታስ ቅንጅቱ ምን አቋም ይወስዳል? ቅንጅት በሁለት እሳት መሀከል ግጭትን እንዴት ማስወገድ እንችላለን?
- የሰኔ አንድ ግድያ፣ የግንቦት 30 የደህንነት ወከባና የሼራተን አዳር፣ ስለ ምርጫ ማጣራት ሒደቱ ሰኔ አንድ በአውሮፓ ህብረት የተጀመረ ውይይት (ግድያው እየተፈጸመ እያለ)
- የአና ጎሜዝ የማጣራት ጎዞና የሁኔታው ጨለማነት፣ ግን ያለው ምርጫ መደራደር ብቻ ነው የሚል ግፊት

(መ) የምርጫ ማጣራት ሒደቱ ሥምምነት

- የሰኔ አንድ ግድያ የፈጠረው ሥነልቦናዊ ድባብ
- የአቶ ሀይሉና የልደቱ የቁም እስር የኢህአዴግ የመደራደሪያ እስትራተጂ (አቶ ሀይሉም ሆነ ልደቱ የድርድሩ አካል አልነበሩም:: ግን በስልክ ግንኙነት ነበር)
- በስምምነት ሰነዱ የ(ERIS (Richard)) ሚና የኢትዮጵያን ተቋማት (በተለይም ምርጫ ቦርድንና ፍርድ ቤቶችን) ነጻ ናቸው ብለን መውሰድ አለብን የሚለው ግትር አቋምና በተቃዋሚዎች በኩል የቀረበው ተቃውሞ::
- የተቃዋሚዎች የምርጫ ቦርድን ቅድመ ማጣሪያ ስልጣንና በማጣራቱም ያለውን ወሳኝ ሚና መቃወም
- ኢህአዴግ፣ (ERIS) እና የአውሮፓ ህብረት ከዚህ ሌላ አማራጭ የለም የሚለው የማያወላዳ አቋም:: የነበረው አማራጭ ወይንም ድርድሩን መተው (ለዚህም ማጣራቱን) ወይንም በዚህ ሁኔታ ቢሆን ማጣራቱን በመሳተፍ የማይሰራ ከሆነ ይህንኑ አሳይቶ መተው የሚሻል መሆኑን መተው:: (ከዚህ በኋላ የእኔ አውሮፓ መሄድና የልደቱ አቋም)
- ስምምነቱና የቀረበው "ቅድመ ሁኔታ"

- ቅድመ ሁኔታው የፈጠረው ችግር፣ የቀረበው ማሻሻያ፣ የበየነ ከበረከት ጋር መወገን::

(ሠ) የምርጫ ማጣራቱ ሂደት

- ማጣራቱ ሂደት ላይ የነበረው የቅንጅት ዝግጅት በቂ ነበር? ጊዜስ ነበር?
- በምርጫ ማጣራቱ ኢህዴግና ምርጫ ቦርድ የፈለጉትን ቦታ ሁሉ ለማግኘትና ለዚህም አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ (በግልጽና አይን ባወጣ መንገድ) መዘጋጀታቸው::
- ማጣራቱ ፍጹም ቀልድ መሆኑ ገና ማጣራት በተጀመረ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ በሁሉም ቦታዎች ግልጽ እየሆነ መምጣቱ:: ቅንጅቱ የላካቸው አጣሪ ቡድኖች በገዛ ፈቃዳቸው የዚህ ቀልድ ተሳታፊ አንሆንም ብለው ጥለው መውጣታቸው (በተለይ ጠበቆች) (አልቡኮ፣ ባቲ፣ሲዳማ፣ጅማ ... ወዘተ ሁሉም ቦታ)
- ቅንጅቱ ማጣራቱን ጥሎ ይውጣ ወይንስ ይቀጥል? በቅንጅት የነበሩ ውይይቶች (ለውጤት ሣይሆን በተለይ ለአለም አቀፉ ህብረተሰብ ማጋለጫ እንጠቀምበት)
- ማጣራቱ ምንም ዋጋ እንደሌለውና ያለው አማራጭ በ299 ቦታዎች ሁሉ ድጋሚ ምርጫ ማድረግ ነው የሚል የህብረትና የቅንጅት የጋራ አቋምና መግለጫ::
- ቅንጅትና ሕብረት ያቀረቧቸው ባለ10 ነጥብ የድርድር ሀሳቦች (ስለ እስረኞች፣ ስለሜዲያ፣ ... ወዘተ)
- ድጋሚ ምርጫ እንዳይካሔድ በፍርድ ቤት በኩል የተደረገው ሙከራና የፍርድ ቤት ነፃ አለመሆን መጋለጥ

(ረ) ከምርጫ ማጣራት ሂደቱ ከንቱነት በኋላ ወዴት? ችግሩን እንዴት በሰላማዊ መንገድ መፍታት ይቻላል?

(ረ-1) በምርጫ ማጣራቱ ሂደት የኢህአዴግ አቋም ግልፅ መሆን (በስልጣን ላይ ለመቆየት የዴሞክራሲ ጭንብሉን እንኳን ማድረግ እንደማይፈልግና በሐይልም ቢሆን ለመቆየት እንደወሰነ)

(ረ-2) ይህ አቋም ለዲፕሎማሲያዊው ማህበረሰብ ግልፅ መሆን፤ ግጭት ለማስወገድና ወደ ፍጹም አምባገነንነት ከመግባት ተቃዋሚዎችን ገፍቶ ፓርላማ ማስገባት ይሻላል የሚለው በተለይ የአሜሪከ አቋም::

(ረ-3) በቅንጅትና በህብረት የቀረበው አቋም:- በሰላምና በዴሞክራሲ መሀል የቀረበው የኢህአዴግ አማራጭ:: የቅንጅትና የህብረት የጥምር መንግስት አማራጭ

(ረ-4) ይህ ግጭትን ሊያድን ይችላል የሚለው ተስፋ (ከአንዳንድ የኢህአዴግ ደጋፊዎችም ጭምር መለስተኛ ድጋፍ ማግኘት (ለምሳሌ የሪፖርተር ርዕሰ አንቀጽ) ግን የኢህአዴግ ፍጹም እምቢተኝነት

(ረ-5) በቅንጅትና በህብረቱ በኩል የህዝብ ድምጽ ይከበር የሚለው አቋም በኢህአዴግ ተቀባይነት ከጣና በህዝቡ በኩል ግን ግፊቱ ከጠነከረ ከሰላማዊ ትግል በቀር ምንም አማራጭ የለም የሚል ግንዛቤ እያደር እየተጠናከረ መሔዱ (በተለይ ሕብረት ከጥምር መንግስት ሌላ ወይ ፍንክች የሚለው አቋሙ)

(ረ-6) ጥምር መንግሥት ባይቀበል ሌላ ቢቀር የወደፊቱን የዴሞክራሲ ሂደት በሚያረጋግጡ ጉዳዮች ላይ ሥምምነት ይድረስ የሚል የለዘበ አቋም በቅንጅት በኩል ለዲፕሎማሲው ማህበረሰብ፣ (ቲም፣ ኢነግሪድ፣ በራዚል፣ ...ወዘተ) ለኢህአዴግ ባለማሎች (ግርማ ብሩ፣ ሙላቱ) እንዲሁም ይሰሚቸዋል ለሚባሉ ገለልተኛ አካሎች (IAG፣ ሪፖርተር፣ ... ወዘተ) የተደረጉ ሙከራዎች: የኢህአዴግ ፍጹም እምቢ ባይነት::

(ረ-7) በዚህ ጉዳይ ላይ ከጠቅላይ ሚኒስተሩ ጋር የተደረገ የመጀመሪያ ውይይት (በየነ፣ ብርሀኑ)፤ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ማስጠንቀቂያ::

(ረ-8) ቅንጅት፣ ህብረት፣ የፓርላማ መግባት ጥያቄ

- ቅንጅት ከታዋቂ ግለሰቦች ጋር በጉዳዩ ላይ መወያት (3 ዙር ውይይት በአይቤክስ ሆቴል
- ቅንጅት ከህዝብ ጋር መወያየቱን አስፈላጊነት አመነበት:: ግን ውይይቱ በተቻለ መጠን ከፓርላማ መግባት ለመግባት ጋር እንዳይያያዝና ይህም አመራሩ ብዙ ነገር አይቶ የሚወስነው መሆኑ ለህዝቡ ግንዛቤ ማስጨበጥ ነበር ፍላጎቱ::
- የህዝቡ ግፊት ግን በጣም ጠንከራ ነበር
- የሲቪክ ማህበረሰብ አቋም
- የተለያዩ አደራዳሪዎች (ሽማግሌዎች) ሙከራና የቅንጅት እሺ ባይነትና የመንግስት ፍጹም እምቢ ባይነት
- ህብረት አካባቢ ፓርላማ መግባትን የመርህ ጉዳይ ሣይሆን የህልውና ጥያቄ አድርጎ እንደሚታይ ግልፅ ሆነ:: (መራራም በየነም ለመግባት እንደወሰኑ ግን እስከዚያ መታገል?
- ቅንጅት ከፓርላማ ጥያቄ ለረጅም ጊዜ ሸሸ፣ ጥያቄውን ለማስፋት ሞከረ

(ረ-9) ሕጋዊና ሰላማዊ ትግል የፓርላማ መግባት ውሳኔ ከመወሰኑ በፊት

- ቅንጅት ወደ ግጭት የማያመሩ የትግል ስልቶች እያሰበ እግረ መንገዱን ግን የድርድቱ ማጠናከሪያ የውህደት ጉዳዩን አስፈላጊነትና አስቸከይነት አመነበት፣ በዚህም ዙሪያ እንቅስቃሴ ጀመረ
- በዚህ መሀል የህብረት ስብሰባ በአሜሪከ ለመስከረም 22 ስብሰባ ጠራ:: ቅንጅቱ ወሳኔውን ቢጠላውም (በተለይ ሣይማከር መደረጉን አንዳንድ ማስተካከያዎች አድርጎ አብሮ መግፋት ነበረበት:: የጋራ ኮሚቴ ተቋቋመ ከሰልፉ በፊት ጉባኤውን ለማድረግና የጉባኤው ተወከዮች እነማን እንደሚሆኑ ተወሰነ
- ኢህአዴግ ማንኛውንም የቤት ውሥጥም ከቤት ውጭም የሚደረግ ስብሰባ ከለከለ
- ሆቴሎች አዳራሽ እንዳያከራዩ ተከለከሉ::

(1-10) መንግስት ከልክሎ ስብሰባ ማድረግ ወደ ግጭት ይወስዳል የሚለው የቅንጅት ፍርሀት

- ከመንግስት ጋር የማያጋጭ የሰላማዊ ትግል ጥሪ - የ3 ቀናት የቤት መቆየት ጥሪ
- ጥሪው የተደረሰበት ጊዜ በአጋጣሚ የአፍሪከ ህብረት ስብሰባ የነበረበት መሆኑ (በቅንጅት በኩል በፍጹም ተረስቶ ነበር)
- የኢህአዴግ መደናገጥና ለውይይት ፍላጎት ማሳየት: በአሜሪካ ኤምባሲ ሙሉ ቀን የፈጀ ውይይትና የተደረሰበት ስምምነት: (ሥልጣናቸሁን አንፈልግም ግን በዴሞክራሲ ሂደቱ ዙሪያ መደራደር - የብርሃኑና የበየነ ሀሳብ? ወይስ የሁሉም?) የቤት መቆየት ጥሪውን ተውትና እንወያይ:
- ኢሕአዴግ ውይይት በእርግጥ ፈልጎ ነው ወይንስ ጊዜ መግዢያ ነው?
- ቅንጅት በሮ ሥራ አስፈጻሚው ያደረገው ረጅም ውይይት ከዲፐሎማሲያዊ ማህበረሰቡና ጋዜጠኞችም እየጠበቁ ባለበት:: በመከራ የተደረሰ ስምምነት::
- ከጠ/ሚ መለስ ጋር እሁድ እለት ስለድርድሩ መጀመር የተደረገ ውይይት
- በምንም ጉዳይ ላይ መወያየት እንችላለን (ሕገ መንግሥቱን እስከተከተልን ድረስ)
- ቅንጅት በድርድሩ በማን ይወከል? (ብርሃኑ ይኑር አይኑር?)
- የመደራደሪያ ሀሳቡ ምን ይሁን? (በብርሃኑ የቀረበ ፅሁፍና የመጨረሻው የሥራ አስፈጻሚ ስምምነት

(ሰ) ከአቶ በረከት ጋር የተደረገው የፓርላማ ውይይት መክሸፍ

(ሰ-1) ከመነሻው በሚዲያ አጠቃቀም መግለጫ የተጀመረው ሽኩቻ (ግማሽ ቀን የወሰደ)
- እውነተኛ ስምምነት መፈለግ ወይንስ ተራ ብልጥነት?

(ሰ-2) የድርድር ፎርማሊቲዎች ላይ ስምምነት (ማን ይናገር? የሌላው ሚና ምንድን ነው? ለምን ያህል ጊዜ ይናገር? የአደራዳሪዎች ሚና ምን ይሁን እነማን ይሁኑ? ጋዜጣዊ መግለጫ እንዴት ይሰጥ? ማን ስብሰባውን ይምራ?

(ሰ-3) የሁለተኛው (ማክሰኞ) ቀን ዝርዝር ውይይቶች የድርድር አጀንዳዎቹ ምን ይሁኑ?

- በቅንጅትና በህብረት የቀረቡ ዋና ዋና የመደርደሪያ አጀንዳዎች
- በኢህአዴግ የቀረቡ አጀንዳዎች
- ኢህአዴግ ከፈለጋቸው ጉዳዮች (ከስምንቱ) በቀር በሌሎች አጀንዳዎች ላይ አልወያይም የሚለው ግትር አቋም ይህን አቋም ለማስቀየር የተደረጉ ሙከራዎች (በዲፕሎማቶቹም በግል በረከትን በመጠየቅም አለመሳካት)
- በነጋታው እሮብ ይህንኑ ጉዳይ ለመፍታት ከጠ/ሚ መለስ ጋር በአሜሪከ አምባሳደር ጠያቂነት የተደረገ ውይይት ይህም ቢሆን ምንም ወጤት ሊያስገኝ አለመቻሉ
- የአቶ መለስ (constituency Analysis) አደገኛ ቦዘኔው እንጂ የእናንተ (constituency ) እንድትገቡ ይፈልጋል
- ውይይቱ ሊቀጥል አልቻለም። ይህንኑ በተመለከተ ቅንጅቱ በጉዳዩ ላይ ከላእላይ ምክር ቤቱ ጋር ለመወያየት በነጋታው (ሀሙስ) ጠዋት ቀጠሮ ይይዛል። ይህንን ውሳኔ ይዞ በድርድሩ መቀጠል አለመቀጠሉን ለመወያየት ተደራዳሪዎች ሐሙስ ከሰአት ቀጠሮ
- የቅንጅት ላእላይ ም/ቤት በተለይ በምርጫው መጭበርበር ጉዳይ በሽግግር መንግሥት የምርጫ ቦርድ (Restructuring) ላይ ውይይት ካልተደረገ ድርድሩ እንዲቋረጥ ይወስናል
- በዚሁ ድርድሩ ይቋረጣል

(ሸ) ከድርድር መፍረስ በኋላ የፓርላማ መግባት ጥያቄ አፍጥጦ መጣ

(ሸ-1) ፓርላማ የመግባት ጥያቄ ለምን ትልቅ ጥያቄ ሆነ? ለኢህአዴግ? ለለጋሽ አገሮች? ለተቀዋሚዎች? በተለይ ለህዝቡ በአጠቃላይ (ምክንያቶቹ ይለያያሉ?)

(ሸ-2) ፓርላማ የመግባት ያለመግባት ውይይት ሂደት በቅንጅት

- የደህንነት ውይይቶችን መቅዳት (በኢፍቲን መውጣት) ውይይቱን እስከ መጨረሻው ሰአት ድረስ ለመግፋት ምክንያት?

- ቅዳሜ ሙሉቀን የነበረው ውይይት ሂደት፣ ያለመከፋፈል አስፈላጊነትና የድምጽ አሰጣጥ አካሄድ፣ ውሳኔያችንን የሚገፋው ምክንያት ምንድን ነው? የዴሞክራሲ ግንባታ?
- ፓርላማ መግባት ከህዝቡ ጋር ያጣላናል? ኢህአዴግ ቅንጅቱን ለማጥፋት ከወሰነ ፓርላማ መግባት እራስን ለማዳን ወይንስ ለዲሞክራሲ ግንባታ? ከህዝብ ጋር ተጣልቶ እራስን ማዳን ይቻላል? ኢህአዴግ ቅንጅቱን ከህዝብ አጣልቶ ነጥሎ ለመምታት አይመቸውም?
- የቅዳሜ ማታ የደህንነት ጠንከራ እንቅስቃሴ (የእኔ ቤት የራት ግብዣና ከዚያ በኋላ) ውሳኔያችንን አቅጣጫ ለማስያዝ የተደረገው የማስፈራራት እርምጃ ተቃራኒውን ውጤት አመጣ
- በፓርላማ መግባት ጉዳይ ከዲፕሎማቶችና ከኮፊ አናን ጋር የተደረገ ወይይት
- በፓርላማ መግባት ጉዳይ የመጨረሻው (እሁድ) ውሳኔና የስምምነቱ አይነት
- ፓርላማ መግባትና አዲስ አበባ - ሁለቱ የግድ ይያያዛሉ?
- የልደቱ የብልጥነት አካሄድ በሁለቱም ላይ

(ቀ) ፓርላማ ካልተገባ ትግሉ እንዴት ይቀጥላል?

(ቀ-1) የቅንጅትን ውህደት ሕጋዊ ማድረግ አስቸኳይ (የምርጫ ቦርድ የሜዲያ አስተያየት)

- የልደቱ የመጨረሻና ወሳኝ የአፍራሽነት እርምጃ
- የልደቱ ችግር ምንጩ ምንድን ነው? (የኢህአዴግ የበላይነት ወይንስ ያልተገራ እራስ ወዳድነት? የተለያዩ አስተሳሰቦች በቅንጅት ውስጥ
- ልደቱ ያቀረበው ሀሳብ አሳማኝ ያልሆነው የቀረበው ምክንያት እውነተኛው ምክንያት ስላልሆነ ነው፡፡ እውነተኛው ምክንያት ፊት ለፊት መቅረብ ስለማይችል
- የቅንጅት የልደቱን ጥያቄና እርምጃ ያስተናገደበት መንገድ

(ቀ-2) የቅንጅቱ አመራር አካሔድ አንዳንድ ችግሮች

- አመራር የስራ ባህል: ውሳኔ አሰጣጥና የውሳኔ ተግባራዊነት መከታተል ችግር
- ሥራ አስፈጻሚ ውሳኔ ሰጪ እንጂ ውሳኔ ተከታትሎ አስፈጻሚ አልነበረም (ትልቅ ክፍተት)
- የስራ ክፍፍል ችግሮች: የደህንነት እንቅስቃሴ የፈጠረው ችግር ወይንስ ከዚያ በላይ?
- ለሚያውቀውና ለሚጠብቀው ሁኔታ መዘጋጀት አለመቻል፣ የድርጅታዊ አባልነት (Organizational Paralysis)

(ቀ-3) የሰላማዊና ህጋዊ ትግል ጥሪ አላማና ግብ (ምንም ምርጫ ያልነበረው አካሄድ)

- በተቻለ መጠን ሰላማዊ እንዲሆን መጣር
- የመንግስትን ጉንተላ ለመከላከል ህዝብና መንግስት በጋራ የማይገናኙባቸውን መንገዶች መሻት
- ግቡ ስምንቱን ነጥቦች መንግስት (ኢህአዴግ) እንዲቀበል መጣር እንጂ ከዚያ ያለፈ ምንም አላማ የሌለው ብቻ ሳይሆን እንደምታውም እንዳይኖረው መጠንቀቅ
- የኢህአዴግ የዘወትር የፈጠራ ክስ ለማጨንገፍ መሞከር (ሕገ መንግስታዊ መንግስትን መጣል፣ የዘር ግጭት ... ወዘተ)
- የሙስሊም አመት በአልን ማሳለፍ - ጊዜ መግዛትም ፖለቲካዊም
- የውሳኔው በጋዜጦች በድብቅ መተላለፍና ይህም የፈጠረው ድንጋጤ

(ቀ-4) መንግስት ምን ሊያደርግ ይችላል?

- አጠቃላይ የአፈና እርምጃ (አመራሩን ማሰር ጨምሮ) እንደሚወስድ ተጠብቋል
- ሆን ብሎ ግጭት ይጎነትላል (Provoke) የሚል ግምት ግን ብዙ አልነበረም
- ኢህአዴግ የወሰደው እርምጃ

  * የሰኞ ሁኔታ: የክላክስ ማሰማቱ እርምጃ አልተሳካም
  * የማክሰኞ - ጠዋት ግጭቶች ተከስተዋል መባሉና ይህ እንዳይሆንና ህዝቡ በመንግስት እንዳይተነኮስ የተሰጠ የቅንጅት መግለጫ

- ጥቅምት 22 የጨለማ ቀን
- ቅንጅት ሌላ አማራጭ ነበረው?

(በ) የክፍል 111 መደምደሚያ

- የኢህአዴግ በቅንጅት ላይ የሚያቀርባቸው ክሶች መሰረት በነራቸው?
- ቅንጅት በግልጽ ከሚለው ሌላ ድብቅ አላማ ነበረው? ኢህአዴግ ለምን አለው ብሎ ሰበ? የቅንጅት ለኢህአዴግ ስለላ የሰጠው መልስ ይህን ያንጸባርቃል (ምንም ይህ ነው የሚባል እርምጃ አለመውሰዱ)
- ኢህአዴግ ቅንጅትን ለምን እንደ ዋና ጠላት አየው? ፍርሀቱ መሰረት ነበረው?
- ከቅንጅት በፊት የነበሩ አስተሳሰቦች ምንም ሆኑ ምን ከቅንጅቱ መመስረት በኋላ ያለው አስተሳሰብ የቀድሞውን አሸንፎ ነበር አንዳንድ ድርጅታዊ ቅሪቶች ቢኖሩም::

## ክፍል IV፡ የኢህዴግ እርምጃና የኢትዮጵያ የወደፊት እጣ

መግቢያ ኢህአዴግ የወሰደው እርምጃ በብዙ ገጽታው (ከራሱም ጥቅም አንጻር) ግራ የሚገባ ስለሆነ እንዴት እወጣዋለሁ የሚል ሥሌት ነው?

(1) የኢህአዴግ ሥሌት

(ሀ) ቅንጅቱን ማጥፋት - በጉልበት

- ቅንጅቱ እያለ መኖር አልችልም የሚለው እምነት መሰረቱ ምንድን ነው?
- ቅንጅቱን እንደ ድርጅት ማጥፋት ይቻላል፡- እንደ ሌሎች ድርጅቶች መቆጣጠር የምችለው አይደለም (የኢህአዴግ ድርጅቶችን የመከፋፈልና የማዳከም አባዜ)
- ቅንጅቱ ከጠፋ የድርጅቱ መንፈስ የጠፋል?
- ድርጅቱ ድጋፍ ጊዜያዊ ነው የሚለው ስሌት (ድርጅቱም አዲስ ስለሆነ)

(ለ) ኢህአዴግ በጉልበት ላይ ያለው መመካት - ከራሱ ታሪክ አንፃር የሚገርም ነው

- በራሱ ወታደራዊ ሃይልና በወታደሩ አንድነትና ዲሲፕሊን ያለው እምነት፡ አሳሳች ጊዜያዊ ስሌት
- በጉልበት የሚያስፈልገው ለአጭር ጊዜ ነው ከዚያ ሁሉን አረጋጋዋለሁ የሚለው ስሌት
- በህዝቡ "ፈሪነት" ላይ ያለው እምነት
- በአብዛኛውን ሕዝብ በገንዘብና በጊዜያዊ ፍላጎቱ መደለል ይቻላል የሚለው እምነት (በሰዎች ድክመት መጠቀም ይቻላል ይገባልም የሚለው የአምባገነኖች ስሌትና የዚህ ስሌት ከእድገት ጋር ያለው ተቃርኖ)

(ሐ) ኢህአዴግ በዘር ፖለቲካ (መከፋፈል) ላይ ያለው እምነት

- አሁንም ህዝቡን በዘር ፖለቲካ (ጭቁንና ጨቋኝ ብሔር) መከፋፈል ይቻላል ጭቁን ብሄሮች ከኔ ጋር ናቸው፡ ቅንጅት የአማራ አቀኞች ስብስብ ወይም የነሱ ጥገኞች ናቸው የሚለው ፕሮፖጋንዳ ይሰራል የሚለው እምነት
- የኦሮሞ የብረሄርተኛ ፖለቲካ በኢህአዴግ ስሌት ላይ ያመጣው ቀውስ

(መ) የኢትዮጵያ ሕብረተስብ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ እምብዛም አይጠነቀቅም የሚለው ሥሌት

- ዋናው የህዝቡ ትኩረት ኢኮኖሚው ነው እሱን ደግሞ ማሻሻል እችላለሁ የሚለው ግምት
- ሌላው ትኩረት ሰላምና መረጋጋት ነው እሱንም በጉልበት አመጣለሁ የሚለው ስሌት

(ሠ) ኢህአዴግና የአለም አቀፍ ፖለቲካ ስሌት

- እርዳታ ሰጪዎች ዋና የሚከተሉት የራሳቸውን ጥቅም ነው፡ (ሸብርተኝነትን መዋጋት?) ዴሞክራሲ ዝም ብሎ የፕሮፖጋንዳ ወሬ ነው የሚለው ስሌት (የሀብታም ሀገሮች የሲቪክ ማህበረሰብ እንቅስቃሴን ከስሌት ያላስገባ)
- በኢትዮጵያ ደግሞ ዋና ትኩረታቸው ድህነትን ማጥፋት ነው ስለሆነም በፖለቲካ ምክንያት (ዴሞክራሲ ስለሌለ) የገንዘብ እርዳታ አያቆሙም የሚለው ግምት
- ፈረንጆች እኛን (ጥቁሮችን፣ አፍሪካውያንን) ስለሚንቁን ብዙ አይጠብቁብንም፣ ዴሞክራሲም ጥሩ ነገር ቢሆንም በአፍሪካ አገሮች በቶሎ የሚመጣ ሥላልሆነ ጭቆናው ግልጽና አይን ያወጣ እስካልሆነ ድረስ ብዙ ግፊት አይኖርብንም
- የፈረንጆች ዋና ፍርሀት አለመረጋጋት (instability) ነው፣ መረጋጋትን ደግሞ ከመንግሥት ጋር ስለሚያያይዙት መንግሥትን ሙሉ ለሙሉ አይቃወሙም
- የየትም አገር መንግሥቶች ለመንግሥት (State) ክብር አላቸው፣ ትንሽም ቢሆን በሉአላዊነት ያምናሉ
- ፈረንጆች ተቀዋሚዎችን አያውቋቸውም፣ ስለዚህ አያምኗቸውም፡፡ በአንፃሩ መለስን ይወዱታል፣ ያከብሩታል፡፡
- ፈረንጆች "ካልፈለጋችሁ ተውት" የሚላቸውን የኢሣያስ ዓይነት መንግሥት ያከብራሉ፡፡ ስለዚህ ሌላው አልሰራ ካለ በሱ እንጠቀማለን፡፡

## 2. የኢህአዴግ ስሌት በእርግጥ መረጋጋትንና ሰላምን ያመጣል? ኢህአዴግን በስልጣን ያቆያል?

መግቢያ፡- ኢህአዴግ የደረሰበት የአገዛዝ ቀውስ በጣም ስር የሰደደ (Substantive and deep rooted) ነው፡፡ እየሰጠ ያለው ግን ጊዜያዊ ትንንሽ እሳቶችን ማጥፋት፣ ይህንንም ሲያደርግ ዋናውን ችግር አለመመለሱ ብቻ ሳይሆን የደኑን አጠቃላይ ቃጠሎ የሚያባብስ ነው፡፡ እያደር ችግሩን እያባባሰ ኢህአዴግን የመፍትሔው አካል በፍፁም እንዳይሆን እያደረገው ነው፡፡ ያልተመለሱት የኢህአዴግ አራት መሰረታዊ ቀወሶችን ማየት ይበጃል፡-

(ሀ) የኢህአዴግ ርእዮተ አለማዊ ቀውስ

- ኢህአዴግ እንደ ድርጅት የሚመራበትና የሚያምንበት ርዕዮተ አለም የለውም፣ ወይንም የሚያምንበትን ፊት ለፊት አውጥቶ ሕዝቡን ሊያሰባስብበት አልቻለም፡፡

- የሚያምንበትንና የሚያውቀውን “ሶሺያሊስት” እምነቱን ፊት ለፊት ሊያወጣው አልቻለም፣ ስለዚህም ካድሬዎቹ ህዝቡን የሚሰበስቡት (ነፃ ገበያ፣ ዴሞክራሲ፣ ... ወዘተ) የማያምኑበትን ነው::
- ስለዚህም የገባበት የዴሞክራሲ ጨዋታ የማያውቅበት ስለሆነ አካሄዱ በሙሉ ልብ አይደለም (ad-hoc) ይህም ስለሚያስታውቅበትና (በጣም ብዙ ስለሚሳሳት) በዚህ በአዲሱ ጨዋታ የበለጡ የተካኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ይጋጫል:: አጠቃላይ እስትራተጂካዊ አቅጣጫም የለውም::
- ኢህአዴግና የመደብ ትግል ለማን ነው የቆመው?

(ለ) የኢህአዴግ የብሄርተኝነት ቀውስ

- ዘውጌ ብሄርተኝነትን ቅስቀሳ አፋፍሞ፣ ከፍተኛ የፕሮፖጋንዳ ሽፋን ሰጥቶ፣ ግን ሙሉ ለሙሉ መቆጣጠር ይቻላል?
- ዘውጌ ብሄርተኛነትና የአጋር አንድነት ተሸካሚው ድርጅት አንድ ይሆናል?
- የጨቋኝና የጭቁን ትርጉም፣ የጭቁኑን መመሪያ (cause) የሚሸከምለት ማን ነው? (ስሜታዊ ፕሮፖጋንዳ ከፊል (ነፍጠኛነት፣ ኢንተርሀምዌይነት፣ ... ወዘተ) ጭቁን ብሄሮች እራሳቸው ይደራጃሉ ወይንስ ኢህአዴግ ያደራጃቸዋል? ለብሄር ድርጅቶች ሌላ የብሄር ድርጅት መፍጠር ያመጣው ቀውስ
- የኢህአዴግ የብሄርተኝነት ቀውስ ሁነኛ መግለጫ፣ የኦሮሞ ሕዝብ ስሜት ኦነግና ኦብኮ
- ኢህአዴግና የአማራው ህዝብ፣ እንደ ብሄር እየሰደብነውና ጨቋኝ እያልከው እንዲደግፍህ ትሻለህ?
- የኢትዮጵያ መበታተን እንደማስፈራሪያ፣ እኔን ከደገፋችሁ አገር ትኖራለች አለበለዚያ ትበታተናለች የሚያስኬድ ፕሮፖጋንዳ ነው? ሲመች አንድ ላይ መግዛት ሣይመች መገንጠል የሚያስኬድ እስትራተጂ

(ሐ) የኢህአዴግ የእድገት ቀውስ

- የእድገት መሰረት ማን ነው? መንግሥት ወይንስ ሕዝብ (ግለሰብ፣ ሲቪክ ማህበረሰብ፣ ከበርቴ፣ .. ወዘተ)
- የኢኮኖሚና የፖለቲካ ፍጥጫ፣ ለመግዛት የሰዎችን (ዜጎችን) መጥፎ ባህርይ መፈለግ (አድርባይነት፣ አጭበርባሪነት ፣ በነፃ አለማሰብ... ወዘተ) ለእድገት ደግሞ የዜጎችን ጠንክራ ጎን መፈለግ (ታታሪነት፣ በራስ መተማመን ፣ ሀቀኝነት ፣ ነጻነት ... ወዘተ)

- ኢኮኖሚውን ለመቆጣጠር መፈለግ፣ ነጻ ድርጅቶችን አለማመን ስለዚህ የእድገት መሠረት የሚሆን ጠንካራ አካል (strong porivie sector) እንዳይኖር መከላከል፣ ኢኮኖሚውን ቢቻል በፓርቲ ድርጅቶች ለመቆጣጠር መሞከር
- አገራዊ ብሔርተኛነትና የኢኮኖሚ እድገት (ኢህአዴግ ቻይናን ለመሆን ያለው ፍላጎት ለምን እንደማይሰራ)

(መ) የኢህአዴግ የዴሞክራሲ ቀውስ

- የአንድ ፓርቲ የሚቆጣጠረው (dominant) ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ቅዠት (ኢትዮጵያ-ጃፓን? ኢትዮጵያ - ሜክሲኮ)
- ዴሞክራሲ፣ ዘውጌ ብሔርተኝነትና የአናሳ ብሄር መሪነት ይሰራል?
- የዲሞክራሲ ፕሮፖጋንዳ የህዝብ ተስፋ (expectation) ለዘላቂው በፍጹም የማይጣጣሙ ነገሮች
- ዴሞክራሲና፣ ሰላምና የጉልበት አገዛዝ አሁንም በፍጹም የማይጣጣሙ አካሄዶች
- ዴሞክራሲና የዴሞክራሲ ተቋማት:: ተቋማትን ለኢዲሞክራሲያዊ አገዛዝ መጠቀም የበለጠ ዘላቂ ችግር ያመጣል:: (አሳፋሪው የኢህአዴግ ፍርድቤቶችን ፣ ምርጫ ቦርድን፣ ፓርላማን... ወዘተ) ለአገዛዝ መጠቀም የእነኝህን ተቋሞች ፍጹም ተቀባይነት ማሳጣት
- ፈረንጆችን ማጭበርበር እስከመቼ ይቻላል? ያን ያህል ሞኞችና የዋሖች ናቸው? ወይንስ አውቀው የሚታለሉ?

(ሠ) ኢህአዴግና የጦር ሐይሉ

- በእርግጥ ለሁሌም መሳሪያ ይሆናል?
- የጦሩ አንድነትና የብሄርተኝነት ፖለቲካ
- ጦሩና የፖለቲካ ገለልተኝነት በፕሮፖጋንዳ ደረጃ
- ጦሩና የኢትዮ-ኤርትራ ቀውስ (የጦሩና የፈረንጆቹ ፍላጎት ሲጋጭ)

## (3) ኢህአዴግና ሰላማዊ ትግሉ:-

- የኢህአዴግ እርምጃዎች (አፈናው፣ ጉልበቱ ... ወዘተ) የሚቀለበስ ነው ወይንስ እስከመጨረሻው ይገፋበታል?
- የሚገፋበት ከሆነ በኢትዮጵያ ለዴሞክራሲ የሚደረገው ትግል ምን መልክ ይይዛል? በሰላማዊ ትግል የሚያምኑ እንደ ቅንጅት ያሉ ሀይሎች ከጨዋታው ይወጣሉ?

- የሰላማዊ ትግል ተስፋ ከሞተ በጠመንጃ ----------- ይመጣል? (የጠመንጃ ትግልና ዘውጌ ብሄርተኝነት፣ በጠመንጃ ስልጣን የያዙ እውነት ዴሞክራሲ ያመጣሉ? (የኢህአዴግ ተመክሮ))

## (4) ኢህአዴግና እርዳታ ሰጪዎች

- የኢህአዴግ ምንነት ግልፅ እየሆነ ሲሄድ የለጋሽ አገሮች እምነት ማጣትና ሊወሰዱ የሚችሏቸው እርምጃዎች
- የኢኮኖሚ ማእቀብ መቋቋም የሚችል አገራዊ ኢኮኖሚ በኢትዮጵያ አለ?
- የውጭ እርዳታና የኢትዮጵያ በጀት
- አለመረጋጋትና የውጭ ኢንቨስትመንት
- አለመረጋጋትና የአገር ውስጥ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ
- የፖለቲካ ቀውስ ላይ የኢኮኖሚ ችግር ሲደረብበት (Macro economic crisis)

## (5) ኢትዮጵያ ወዴት?

(ሀ) የኢህአዴግ አጥፊ መንገድ መገታት አለበት

- አሁንም የሰላማዊ ትግል ዋና አማራጭነት ሕዝቡ ውስጥ እንዲሰርጽ ያስፈልጋል
- ለዚህ ትግል ሰፊ የህብረተሰብ ክፍልን ማነቃቃት ያስፈልጋል
- በኢህአዴግ ውስጥ ይህን የጥፋት መንገድ የማይፈልጉ አሉ ብሎ በማመን እነሱን ይህን አጥፊ መንገድ የመቋቋም አካል እንዲሆኑ መጣር ያስፈልጋል።
- በምንም አይነት ወደ እርስ በእርስ ግጭት (በተለይ የብሄር) እንዳያመራ መጠንቀቅ ብቻ ሳይሆን በቀጥታ መከላከል (active preventive measures) ያስፈልጋል።

(ለ) በግልጽ የተቀመጠ አማራጭ ራዕይ ያስፈልጋል

- ምንም የማያወላዳ በዜግነት ላይ የተመሰረተ እውነተኛ ዴሞክራሲ
- የቡድን ባህላዊና ሌሎች ዴሞክራሲያዊ መብቶች ያለምንም መሸራረፍ (አብሮነታችንን በሚያጠናክር መልኩ) መከበራቸውን ማረጋገጥ። የቡድኖች (ብሔሮች) በነጻ የመደራጀት መብት በተግባር።
- የዜጎችን ነጻና ሙሉ ተሳትፎ የሚፈቅድ ብቻ ሳይሆን በዜጎች ነጻነት ላይ የተመሰረተ ጠንከራ አገራዊ ኢኮኖሚ መገንባት ዋና አላማው የሆነ

- ኢትዮጵያውያን ባሉበት ሁሉ ለአገራቸው እድገት የሚሳተፉበትን መንገድና እነሱን ዋና የውጭ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ (ከውጭ ዜጎች ኢንቨስትመንት በበለጠ መልኩ)
- በአጠቃላይ ፖለቲካችንንም ሆነ ኢኮኖሚያችንን ብሎም ማህበራዊ ኑሮአችንን ማዘመን የራዕዩ አጠቃላይ መሰረት መሆኑ
- የዘመናዊነትን መሠረት ጠልቶ የገባ የግለሰብ ነጻነት ነው፡፡ በሱ መደራደር አይቻልም፡፡

(ሐ) የክፍል IV ማጠቃለያ

- የፖለቲካ ስልጣን በራሱ ግብ ሲሆን የሚያመጣውን ጣጣ አይተናል፡፡ ኢትዮጵያም እንድትኖር ከዚህ አጉል ስሌት ፖለቲካው መውጣት አለበት
- የፖለቲካ ስልጣን ከራሱ በላይ ለሆነ አላማ ሲውል ጠንካራ የለውጥና የእድግት ሀይል ይሆናል
- የጥላቻ ፖለቲካ በዚሁ ማብቃት አለበት
- የአጭር ጊዜው እንጂ የረጅም ጊዜው የኢትዮጵያ ተስፋ ብሩህ ነው፡፡ ይህን የረጅም ጊዜ ተስፋ ለመጠበቅ የአጭር ጊዜ እንቅስቃሴዎች (የፖለቲካ) የረጅሙን ራዕይና ተስፋ የሚጎዱ መሆን የለባቸውም፡፡ ለዚህም የተቃዋሚ ፖለቲካ ሃይሎች ከቂምና ከጥላቻ መራቅ አለባቸው፡፡